# ምዕራፍ 11

## አገልጋይና ጊዜው

ጊዜ ወርቅ ነው። የአንድ አገልጋይ የአመራር ችሎታ በሥራ ሰዓቱ በሚያከናውናቸው ድርጊቶች ይገለጻል። የአንድ ወጣት ባሕርይና ተግባር የሚቀረጹት በትርፍ ጊዜው በሚሠራቸው ሥራዎችና በሚተባበራቸው ሰዎች ነው። በትምህርትና በሥራ የሚያሳልፋቸው ሰዓቶች በእርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ ጊዜያት አይደሉም፣ እነዚህን ጊዜያት በእነዚህ ሥፍራዎች ማሳለፍ ያለበት መሆኑ የታወቀ ነው፤ ከእነዚህ ጊዜያት በፊትም ሆነ በኋላ የሚሠራቸውን ሥራዎች ግን እራሱ በራሱ መወሰን ይችላል። ለሥራ፥ ለምግብና ለእንቅልፍ ከሚጠቀምባቸው ጊዜያት ውጪ ያሉትን ሰዓታት የሚያሳልፍባቸው ሁኔታዎች ጥሩ ወይም መጥፎ ሰው ሊያደርጉት ይችላሉ። አንድ ሰው ኑሮውን የሚያሳምሩለትን ወይም የሚበክሉትን ባሕርያት የሚቀስመው በወጣትነቱ ነው። አንድ ሰው ያሉት ትርፍ ጊዜያት መልካም አጋጣሚዎች ወይም አደገኛ ሁኔታዎች ሊፈጥሩለት ይችላሉ። በእያንዳንዱ ቀን ውስጥ ያለችው እያንዳንዷ ደቂቃ የእግዚአብሔር ስጦታ ናት፤ ጊዜ እንድንሠራበት ተለክቶ የተሰጠን በመሆኑ በብልሐትና በቁጠባ ልንሠራበት ይገባል።

ደቂቃዎችና ሰዓታት ብልጽግና ወደ ተሞላውና ወደ ተትረፈረፈ ኑሮ ሊለወጡ ይችላሉ። ሚካኤል አንጀሎ ይህንን እውነት የተቀበለ ሰው ነበር። አንድ ሥራ እንዲሠራ ተገድዶ ይፈጽም በነበረበት ወቅት አንድ ሰው መጣና «እስከ ሞት ድረስ ዋጋ የሚጠይቅህ ሥራህ ሊሆን ይችላል!» የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቶታል። ይህም ታላቅ የጥበብ ሰው «ታዲያ ኑሮ ለምንድን ነው?» ሲል መልሶለታል። ያሉን ሰዓታትና ቀናት እያለፉ በሄዱ ቁጥር ዓላማና ፍሬያማነት በተሞላው መንገድ ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ሕይወታችንን ወሳኝ የሚያደርገው ለዘለቄታው ዕድገታችን የሚሆን ሥራ መሥራት ነው። የጊዜ ዋጋ የሚለካው በርዝመቱ ሳይሆን በሚሰጠው አገልግሎት ነው። ዋጋ ያለው ረዥም ጊዜ መኖራችን ሳይሆን ጊዜያችንን በተሟላና በደኅና ሁኔታ ልንገለገልበት መቻላችን ነው።

ጊዜ ብርቅና ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም እንደ እርሱ የምናባክነው ነገር የለም። ሙሴ ጊዜ በዋጋ ሊለካ የማይችል ታላቅ ነገር መሆኑን ስለተረዳ ጊዜያትን በዓመታት ሳይሆን በቀናት መለካት እንዲችል ጸልዮአል፤ መዝ.90፡12። ያሉንን ቀናት በጥንቃቄ ከተጠቀምንባቸው ዓመታት ለራሳቸው ይጠነቀቃሉ።

«ይህንን አስፈላጊ ሥራ የምሠራበት ጊዜ የለኝም» የሚል ዓረፍተ ነገር አብዛኛውን ጊዜ ከመሪዎች አይሰማም፤ ብዙውን ጊዜ ይህ ምክንያት እውነት አይደለም። ጊዜ የለኝም የሚለው ሰበብ ብልሐት ያጣ ሰው ለማምለጫ የሚጠቀምበት ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ለመፈጸምና ለሕይወታችን ያለውን ዕቅዱን በሥራ ላይ ለማዋል ለሁላችንም በቂ ጊዜ ተሰጥቶናል። በዘመናችን በሰዎች ሁሉ ዘንድ የሚሠራበት የብልሐት አነጋገር ጊዜን ማመካኛ ማድረግ ነው። ይህንንም ምክንያት በተደጋጋሚ እንጠቀምበታለን፤ በተደጋጋሚ ስለተጠቀምንበትም ራሳችንን እናታልላለን። ጊዜ የሚያጡ ሥራ የሚበዛባቸው ሰዎች

አይደሉም፤ በየዕለቱ የሚሠሩት ሥራ እጅግ ውስብስብነትና ብልሐት የተሞላው ቢሆንም እንኳ በተጠየቁ ጊዜ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ግልጋሎት ለማበርከት ጥቂት ጊዜ አያጡም። አብዛኛውን ጊዜ ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ የሚሆኑት ሰዎች ብዙ ሥራ ያላቸው ናቸው።

ችግሩ ጊዜ መፈለጉ ሳይሆን ያለንን ጊዜ በሚገባ በመጠቀሙ ላይ ነው። በዓለም ውስጥ እንደሚገኘው እንደማንኛውም ሰው እኩል ጊዜ ያለን መሆናችንን አምነን መቀበል አለብን። የአንዲት ሀገር መሪ እንደ ሌላው ዜጋ ሁሉ በአንድ ቀን ውስጥ 24 ሰዓታት አሉት። ከእኛ የበለጠ ችሎታ ወይም ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ፤ ከእኛ የበለጠ ጊዜ ግን የላቸውም።

በሉቃስ 19:12-27 ውስጥ እንደምንመለከተው እያንዳንዱ ሰው እኩል ገንዘብ ተሰጥቶት እንደነበር ሁሉ ለሁላችንም እኩል ጊዜ ተሰጥቶናል። ጊዜያቸው አሥር እጥፍ ትርፍ እንዲያስገኝ በብልሐት የሚጠቀሙበት ግን በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው። በሉቃስ 19 በተገለጸው ምሳሌ ውስጥ ሁሉም እኩል ችሎታ እንዳልነበራቸው እንመለከታለን። አነስተኛ ችሎታ የነበረው ከፍተኛ ችሎታ ከነበረው ሰው እኩል ታማኝነት ስላሳየ ሁለቱም ተመሳሳይ ሽልማት አገኙ። ችሎታ ያነሰን ስለመሆናችን ተጠያቂዎች ባንሆንም ጊዜያችንን ለማሳለፍ ለምንጠቀምበት ዘዴ ተጠያቂዎች ነን።

ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩት ክርስቲያኖች «ጊዜውን ዋጁ» የሚል ምክር መስጠቱ ጊዜን በመግዛት የራሳችን ልናደርገው የምንችል መሆኑን ማሳየቱ ነበር። ጊዜን በሚገባ መጠቀም ከፍተኛ ዋጋ ይጠይቃል። በሕይወትና በኑሮ ገበያ ጊዜን ዋጋ ቢስ በሆነ ወይም ዋጋ ባለው ነገር፥ ፍሬያማ ወይም ፍሬ ቢስ በሆነ ነገር እንመነዝረዋለን። በጥንቃቄ ዕቅድ የወጣለት ኑሮ አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑ የሚታየው ጊዜን መቆጠብ ስለሚያስችል ነው። ጊዜን በቁጠባ የመጠቀም ችሎታችን ሲዳብር የአኗኗርን ዘዴ እየተማርን ነው ማለት ነው። ይህ ካቃተን ሁሉም ነገር ይሳነናል።

ጊዜ ሊጠፋ ይችላል፤ እንደገና ሊገኝ ግን አይችልም። ጊዜን መጠቀም እንጂ ቋጥሮ ማስቀመጥ አይቻልም፤ ጊዜን አስተላልፎ በሌላ ጊዜ ለመጠቀም አይቻልም። ጊዜ ፍሬያማ በሆነ መንገድ ካልተሠራበት እንደገና ላለመገኘት ጠፍቷል ማለት ነው።

አገልጋይ ከእነዚህ ሐቆች አንጻር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለመምረጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ማለት ነው። የሚያገኛቸውን አጋጣሚዎች ካሉበት ኃላፊነቶች ጋር ዋጋቸውን አዘውትሮ ማነጻጸር ያስፈልገዋል። ተቀዳሚነት ሊሰጣቸው የሚገባ አያሌ ጉዳዮች እያሉ ከእነርሱ በኋላ ሊከናወኑ በሚችሉ ጉዳዮች ጊዜውን ማጥፋት የለበትም። በየዕለቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት በጥንቃቄ የታቀዱ መሆን ይገባቸዋል። የተሻለ ሥራ የመሥራት ጉጉት ካለው ከፍተኛ ጥቅም ያላቸውን ሥራዎች የማስቀደምና ሌሎቹን የማስከተል ችሎታ ሊኖረው ይገባል። በአንድ ሳምንት ውስጥ የሚገኙትን ሰዓታት እንዴት እንዳሳለፋቸው በታማኝነት መመዝገብና የእግዚአብሔር ቃል ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች አንጻር መገምገም ጥሩ ውጤት ያስገኛል። ውጤቱ የሚያስፈነጥዝ ሊሆን ይችላል፤ በመንፈሳዊ ረገድ ዋጋው ሲታይ ደግሞ የሚያስከፋ ሊሆን ይችላል። ይህንን ሙከራ የሚያደርግ ሰው በሕይወቱ ከነበረውና ከተጠቀመበት ፍሬያማ ጊዜ የበለጠ ጊዜ የነበረው መሆኑን በማያጠራጥር መንገድ ይረዳል።

ሰዎች ለእንቅልፍና ለዕረፍት 8 ሰዓታት፥ ለምግባቸውና ከሌሎች ጋር ለመጨዋወት 3 ሰዓታትና በሳምንት ውስጥ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ በየቀኑ 10 ሰዓት በሥራቸውና በጉዞ ላይ ቢያጠፉ በሳምንት ውስጥ ለእነዚህ ጉዳዮች ማከናወኛ ካጠፏቸው ጊዜያት ውጪ ከ35 ሰዓታት የበለጠ ትርፍ ጊዜ ይኖራቸዋል። እነዚህን ሰዓታት ምን ያደርጓቸዋል? በሳምንት ውስጥ ያሏቸውን ሁለት ቀናት የሚያሳልፉት እንዴት ነው? ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበረክተው ግልጋሎት የሚለካው እነዚህን ጊዜያት በሚያሳልፍበት ሁኔታ ነው። ሰው ተራ ወይም ልዩ ግምት የሚሰጣቸው መሆኑን በእነዚህ ሰዓታት ውስጥ ያከናወናቸው ተግባራት ያሳያሉ።

በሥራዋ ታዋቂነትን ያገኘች የአንዲት የወንጌል መልዕክተኛ አባት ጠጪና ሰካራም ነበር። ይህች ሴት በአሥራ አንድ ዓመቷ በአንድ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥራ ትሠራ ጀመር። በዚሁም ወቅት ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ትሠራ ነበር። ሆኖም ይህ ዓይነቱ አድካሚ የሥራ ሁኔታ በዘመኗ የፈጸመችው የማይረሳ ተግባር ራሷን ለማዘጋጀት ትማር ከነበረው ትምህርት ሊያግዳት አልቻለም።

አንድ ሌላ የወንጌል አገልጋይ ደግሞ በሀገሩ ውስጥ ይገኝ በነበረ በአንድ የጥጥ ፋብሪካ ውስጥ ከንጋቱ 12 እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ይሠራ ነበር። ሥራውን የጀመረው በአሥር ዓመቱ ነበር። ለጥናት ሰዓት የለኝም ብሎ ሰበብ ቢፈጥር አይፈረድበትም ነበር። ይሁን እንጂ በነበረው ትርፍ ጊዜ የላቲን ቋንቋ አጠና፤ ዕድሜው አሥራ ስድስት ዓመት ሲሆን የላቲንን ቋንቋ ንባብ ችሎ ነበር። ሃያ ሰባት ዓመት ሞልቶት በነበረበት ወቅት ደግሞ ሕክምናና መንፈሳዊ ትምህርት አጠናቅቆ ነበር።

በዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ከተከናወኑት ከእነዚህ ተግባራት አንጻር ስንመለከተው በኑሯችን ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆነ አንድ ተግባር ማከናወን ስንፈልግ ያለን ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው ማለት አንችልም።

በጊዜው አጠቃቀም የጌታ ኢየሱስ ሕይወት ፍጹም ምሳሌነት አለው። ይኖር የነበረው በርጋታ ነበር፤ ሕዝቡ ዘወትር ከሰው ሲያስጨንቁትም በፍጹም ተቻኩሎ አያውቅም። ዕርዳታውን ፈልገው ወደ እርሱ ለሚመጡ ሰዎች ከእነርሱ ፍላጎት የበለጠና አስፈላጊ ነገር ያለው መሆኑን እንዲረዱ አድርጓል። የዝግተኝነቱንም ምስጢር መረዳት የሚቻለው ሥራውን ያከናውን የነበረው የአባቱን ዕቅድ በመከተል መሆኑን መረዳት ሲቻል ብቻ ነው፤ እያንዳንዱ ሰዓት በዚህ ዕቅድ ውስጥ የታቀፈች ናት። የሚያሳልፋቸው ቀናት በቅድሚያ ዝግጅት የተደረገባቸው ነበሩ፤ ከአባቱ ጋር በሚያደርገው ግንኙነትም የሚናገራቸውን ቃላትና የሚሠራቸውን ሥራዎች ከእርሱ ይቀበላል። ይህንን በማስመልከት በዮሐ.14፡10 «እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል» ብሏል።

ከሁሉ ይልቅ ክርስቶስን የሚያሳስበው የተሰጠውን ሥራ በተሰጠው ሰዓት ውስጥ ማከናወኑ ነበር። በእርሱ ላይ የሚደረጉት ነገሮች በሙሉ የሚፈጸሙት እግዚአብሔር አስቀድሞ ባዘጋጃቸው ጊዜያት መሆኑን በሚገባ ያውቅ ነበር፤ ዮሐ.7፡6፤ 12፡23፤ 27፤ 13፡1፤ 17፡1 ተመልከቱ። አባቱ ባወጣለት ዕቅድ ውስጥ እናቱ እንኳ ጣልቃ እንድትገባ አልተፈቀደላትም፤ በዮሐ.2፡4 «አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ሲል የተናገራት ለዚህ ነው።

ለማርታና ለማርያም የነበረው ጥልቅ ፍቅርና በመሃከላቸው ሊፈጠር ይችል የነበረው አለመግባባት ለሁለት ቀናት እንኳ ያቀደውን ሥራ ከመሥራት ሊያዘገየው አልቻለም፤ ዮሐ.11:6፥ 9። የሚሞትበት ዕለት በተቃረበበት ሰሞን በምድር ላይ እንዴት እንደኖረ ሲመረምር «እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ» ብሎ ተናግሯል፤ ዮሐ.17:4። ኢየሱስ ከፈጸማቸው ሥራዎች ውስጥ የተበላሸ አንድም እንኳ አልነበረም፤ ተገቢ ባልሆነ ችኮላ የተሠራ ሥራ የለም። በጊዜ እጥረት ምክንያትም ሳይሠራ የቀረ ሥራ የለም። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሥራ በሙሉ ፍጹም በሆነ መንገድ እንዲያከናውን በአንድ ቀን ውስጥ ያሉት ሃያ አራት ሰዓታት በቂ ነበሩ።

ኢየሱስ «ቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት አይደለምን?» ብሎ ከተናገረው መረዳት የሚቻለው ይህንኑ ነው። ኢየሱስ የጠየቀው ጥያቄ በአባቱ ዕቅድና በተሰጠው ጊዜ ሥራውን መጨረስ የሚችል መሆኑን ያረጋግጣል። ኢየሱስ የተናገራቸው ቃላት ጊዜ አጭርና በቂ መሆኑን ያሳያሉ። በቀን ውስጥ 24 ሰዓታት አሉ፤ እነዚህም ሙሉ ሰዓታት ናቸው። ኢየሱስ ፍጹም የሆነ የመምረጥ ኃይል የነበረው ለዚህ ነው። ጊዜውን የሚያሳልፈው የሚመለከቱትን ጉዳዮች በማከናወን ነው። የማያስፈልጉ ተግባራት በማከናወን ያጠፋው ምንም ጊዜ አልነበረም። ሰው ሥነ ምግባራዊ ብርታት የሚያገኘው የማይጠቅሙና የማያስፈልጉ ድርጊቶችን ለመፈጸም እምቢተኛ በመሆን ነው።

በአንድ ቀን ውስጥ ያሉትን 12 ሰዓታት ብንዘነጋ በፍርሃት ልንዋጥ እንችላለን። ኑሮ የሚሰጠንን ትምህርቶች መማርና የኑሮ ግዴታዎችን መወጣት የሚያስችሉ 12 ሙሉ ሰዓታት አሉን። እነዚህ ጊዜያት በቂ መሆናቸውን ጌታችን አረጋግጦልናል።

ብጥብጥና ሁከት በበዛበት ዘመን ውስጥ የምንኖር ሰዎች የኢየሱስ የሕይወት ሰላም በምንም ዓይነት ሽብር ሊናጋ አለመቻሉን ስንመለከት ያስደንቀናል። ሥራ በሚበዛበት ሰው ሕይወት ውስጥ በድንገት ሳይታሰቡና ሳይታቀዱ የሚመጡ ችግሮች ውጥረት ሊፈጥሩ ይችላሉ። ኢየሱስ በእግዚአብሔር የታቀደለትን ሕይወት እንዳይኖር ማድረግ የሚችሉ ምንም ጣልቃ ገብ ነገሮች አልነበሩም። አብ እነዚህን ነገሮች በሙሉ አስቀድሞ ተመልክቷቸዋል፤ ስለዚህም በችግሮች እንዳይታወክ አስፈላጊውን ነገር ሊያዘጋጅለት ችሏል ማለት ነው። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ምግብ የሚመገብበት ሰዓት እንኳ አጥቶ ነበር፤ እግዚአብሔር እንዲሠራው ያቀደውን ለመሥራት ግን በቂ ጊዜ ነበረው። አንዳንድ ጊዜ በመንፈሳዊ አገልጋይ ላይ ችግር ሊፈጠር የሚችለው እርሱ እንዲሠራ እግዚአብሔር ያልሰጠውን ሥራ መሥራት በሚሞክርበት ጊዜ ነው። ለዚህ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ብርታት እግዚአብሔር እንዲሰጠው ተስፋ ማድረግ የለበትም።

ሥራ ይበዛበት የነበረ አንድ ሰው ሥራውን እንዳይሠራ ያውኩት የነበሩትን ችግሮች እንዴት ማስወገድ እንደቻለ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «ራስ ወዳድ ከመሆኔ የተነሣ በሚፈጠርብኝ ሥራ ውስጥ እስካለፉት ጥቂት ዓመታት ድረስ በሚያውኩ ነገሮች እቸገር ነበር። ሰዎች ይመጡና ትርፍ ጊዜ ስላለኝ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ይሉኛል። ይህ ደግሞ ለኔ ችግር ይሆንብኝ ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔር በመንገዴ ላይ የሚያጋጥሙኝን ሰዎች ሊልክ እንደሚችል ተረዳሁ። ፊልጶስን ወደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ልኮታል። በርናባስ የጠርሴሱን ሳውልን እንዲጎበኝ ተልኳል። ዛሬም በኛ ጊዜ ተመሳሳይ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። የሚገጥሙን ሰዎች እግዚአብሔር የላካቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

ስለዚህ አንድ ሰው ወደ እኔ በመጣ ቁጥር ወደዚህ ያመጣህ እግዚአብሔር መሆን አለበት፤ እግዚአብሔር ለምን እንደላከህ መረዳት እንድችል እንጸልይ ማለት ጀመርኩ። ይህ አነጋገር ሁለት ጥቅሞች አሉት። እግዚአብሔር በውይይቱ ውስጥ እንዲገባ ስለጋበዝነው ቃለ መጠይቁ በሰውየው ሕይወት ውስጥ ልዩ ሁኔታ ይፈጥራል። በሁለቱ ሰዎች መሃከል የሚደረገውንም ውይይት አጭር ሊያደርገው ይችላል። ሰውየው ያለ ምንም ምክንያት ወይም በልቡ ውስጥ ጥርጣሬ ተፈጥሮ ውይይቱን አሳጥሮ ሊሄድ ይችኩላል። ሥራችሁ መቁረጥ ያለበት በእግዚአብሔር ብቻ ይሁን። ሥራችሁን የሚያቋርጠው ነገር ከእግዚአብሔር የተላከ በመሆኑ ከሥራችሁ እንደ አንዱ ክፍል አድርጋችሁ ቁጠሩት። እግዚአብሔር ሥራችሁን የሚያቋርጠው አሠራራችሁን ለእርሱ የሚመች አድርጎ ሊያስተካክለው ነው። ንቁ ክርስቲያን ሥራውን የሚያቋርጠው ከአምላክ በሚመጡ አንዳንድ ሁኔታዎች ብቻ ነው።»

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ዕቅድ ያለው መሆኑን በሚመለከት ጳውሎስ ከሰጠው ማረጋገጫ ጋር ይስማማሉ፤ እያንዳንዳችን የተፈጠርነው እግዚአብሔር እንድንራመድበት አስቀድሞ ባዘጋጀልን ጎዳና በመሄድ መልካም ሥራዎች ልንሠራ ነው፤ ኤፌ.2፡10። መንፈሳዊ አገልጋይ በየዕለቱ በሚያደርገው ጸሎትና ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው ግንኙነት የእግዚአብሔርን ዕቅድ ዝርዝር ሁኔታ ሊረዳ መሞከር አለበት፤ ሥራውንና ተግባሩንም በዚሁ መሠረት ማቀናበር ይገባዋል። እያንዳንዱ ግማሽ ሰዓት በጠቃሚ ሥራ ውስጥ የራሷ ድርሻ አላት።

አንዳንድ ትላልቅ ድርጅቶች ጊዜያቸውን በደቂቃዎች በመከፋፈል እያንዳንዱ ደቂቃ ፍሬያማ እንድትሆን ከፍተኛ ጥረት ስለሚያደርጉ የበታች ኃላፊዎች ለመጪው ሳምንት ምን ዓይነት ዕቅድ እንዳላቸው ዓርብ ምሽት እንዲያሳውቋቸው ይፈልጋሉ። በዚህ ዓይነቱ አሠራር ልንጠቀም የምንችል ጥቂቶች ነን፤ ከእነዚህ ሰዎች አሠራር ጋር በሚመሳሰል አሠራር ልንጠቀም ከቻልን ግን ተመሳሳይ ጥቅም ልናገኝ እንችላለን። ሳንጠቀምባቸው በከንቱ በምናሳልፋቸው ጊዜያት ምን ያህል ገጾች ማንበብ እንደሚቻል መገንዘብ ያስደንቃል፤ ለማመንም ያስቸግራል። ይህንን ማመን ካዳገታችሁ በመጪው ሳምንት ያለ አንዳች ጥቅም በምታሳልፏቸው ደቂቃዎች ውስጥ ሙከራ አድርጉ።

የሕይወት ታሪኩ በመጽሐፍ የተጻፈ አንድ ምሁር ነበረ። ሩቅ መንገድ በባቡር ሊጓዝ ሲያስብ ዝግጅት ያደርጋል። ባቡሩ ውስጥ አንድ ጥግ ላይ ይቀመጥና እንደ ቤተ መጻሕፍት መደርደሪያ ከተሞላው የዕቃ መያዣው ውስጥ መጽሐፍ ያወጣና በአካባቢው ያለውን ሁኔታ ከምንም ሳይቆጥር ማንበቡን ይቀጥላል። ስብሰባዎች ሲራዘሙ በመካሄድ ላይ ያለው ስብሰባ እስከዚህም በጥሞና ማዳመጥ የማይፈልገው ከሆነ ቦርሳውን ይከፍትና ደብዳቤ ለጻፉለት ሰዎች የመልስ ደብዳቤ መጻፍ ይጀምራል። አንድ ሰው በጣም ጊዜ ቆጣቢ ስለነበረው ስለ አባቱ የሚከተለውን ጽፏል፡- «ጊዜውን በጭራሽ በከንቱ አያጠፋም ነበር፤ ለእርሱ እያንዳንዱ ጊዜ ከፍተኛ ጥቅም ነበራት። አንድ ቀን ከቢሮው ወጥቶ ወደ እኔ መጣና ሀልጂ አሁን ምንም የምትሠራው ሥራ ከሌለህ አብረን ወደ ውጪ ወጥተን መናፈስ እንችላለን፤ እኔ ሃያ ሁለት ደቂቃዎች አሉኝሽ ብሎኝ ወዲያውኑ ከቤት ወጥቶ ጉዞ ጀመረ። እኔም እርሱ ላይ ለመድረስ መሮጥ ነበረብኝ። እንደደረስኩበት መነጋገር ጀመርን። በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታ፥ ስለ መነቃቃት አስፈላጊነትና ስለ ቅድስና አወራልኝ። ቶሎም ወደ ቤታችን ተመለስን።»

አንዳንድ ጊዜ ጥንቁቅ አገልጋይ የሥራ ሰዓታትን እቆጥባለሁ ሲል ሳያስበው የሰዓት እሥረኛ ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህ ስለ ሰዓት ቁጠባ ያለው አመለካከት ሚዛናዊ ሊሆን ይገባል።

ስለ ሰዓት ቁጠባ በቂ መልስ የማይኖረው ከሆነ አስፈላጊ ባልሆኑ ውጥረቶች ውስጥ ገብቶ ሥራውን ይቀጥላል። ግዴታዎቹን ለመወጣት ባለው ኃይሉ በመጠቀም ማናቸውንም ነገር ሠርቻለሁ ካለ በኋላ እንኳ ገና ያልሠራቸው ብዙ ሥራዎች ሊቀሩ ይችላሉ። የእርሱን ዕርዳታ የሚጠይቁ ማናቸውም ጥሪዎች የሚመጡት ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ለሁሉም መልስ መስጠት ጨርሶ አይቻልም። ለየዕለቱ በሚያወጣው ዕቅድ ውስጥ እግዚአብሔርን ለማስገባትና ያንንም ዕቅድ በተቻለው መጠን በሥራ ላይ ለማዋል መሞከር አለበት። ኃላፊነት የሚኖርበት በቁጥጥሩ ሥር ላሉት ነገሮች ብቻ ነው። የተረፈውን ነገር አፍቃሪና ሁሉን ቻይ ለሆነው ለአባቱ በእምነት ሊያስረክብ ይችላል።

የጊዜ ሌባ የሆነው ቸልተኝነት ሰዎች ዘለዓለማዊ እርስታቸውን ከማግኘት እንዲሰናከሉ ሊያደርግ ሰይጣን የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው። የቸልተኝነት ልምድ ያለባቸው አገልጋዮች ፍሬያማ ሠራተኞች የመሆን ደረጃ ላይ ሊደርሱ አይችሉም። ቸልተኝነት ከሰዎች ተፈጥሯዊ ዝንባሌና ጠቃሚ ውሳኔዎችን ከመስጠት የመዘግየት ውስጣዊ ዳተኝነት ጋር ግንኙነት ያለው ኃይልና ብልሐት አለው። ውሳኔዎችን መወሰንና በተግባር ላይ ማዋል ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል። ውሳኔውን በተገቢው ወቅት ሳይሰጥ የሚዘገይ ሰው በራሱ ላይ ተጨማሪ ችግር ይፈጥራል። ዛሬ መሰጠት ያለበት ውሳኔ ከባድ ችግር የሚያመጣ ከሆነ ውሳኔው ለሚቀጥለው ቀን ቢተላለፍም ምንም መፍትሔ አያመጣም፤ እንዲያውም ውሳኔው በመዘግየቱ ለውሳኔው የሚያመቹ ጠቃሚ ሁኔታዎች ለውጥ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ውሳኔውን ከባድ የሚያደርጉት ሁኔታዎች ከነገ ይልቅ ዛሬ ቢቀርቡ ቀለል ሊሉ ይችላሉ።

የብዙ ሰዎችን ሥራ ያማረ ያደረገው «አሁኑኑ ሥራው» የሚለው የተግባር መርሆ ነው። ይህ መመሪያ በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ ሥፍራ ቢያገኝ ተገቢና አስፈላጊ ነው። መሠራት ለሚገባው ሥራ የጊዜ ገደብ መስጠትና በምንም ምክንያት ገደቡን አለማፍረስ ቸልተኝነትን የመቋቋሚያው ትልቅ መንገድ ነው። በተጨማሪ በጥድፊያ መሥራትም አስፈላጊ አይደለም።

በጣም ሥራ የሚበዛበትና ዕድሜውን በሙሉ መጽሐፍ ያነብ የነበረ አንድ ሰው፦ «መጽሐፍ ማንበቢያ ጊዜ ልታገኝ የምትችለው እንዴት ነው?» የሚል ጥያቄ ዘወትር ከጓደኞቹ ይቀርብለት ነበር። እርሱም የሚሰጠው መልስ «ካለኝ ጊዜ የተወሰነውን ለመጽሐፍ ማንበቢያ አውለዋለሁ እንጂ መጽሐፍ ማንበቢያ ትርፍ ጊዜ የለኝም» ብሎ መልስ ሰጥቷል።

# ምዕራፍ 12

## አገልጋይና የማንበብ አስፈላጊነት

«ስትመጣ ... መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ!» 2ጢሞ.4፡13።
ማንበብ ሙሉ፥ መናገር ዝግጁ፥ መጻፍ ደግሞ ሰውን ሚዛናዊ ያደርገዋል።

ጳውሎስ «አስተውለህ አንብብ» በማለት ለጢሞቴዎስ የሰጠው ምክር በዘመኑ የነበሩት ሰዎች የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት የማንበብ ልማድ እንደነበራቸው ያለ ጥርጥር ያመለክታል። የጳውሎስ ትዕዛዛት ሌሎች መጻሕፍትንም ለማንበብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያዘለ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንዲያመጣለት የፈለጋቸው መጻሕፍት የአይሁድን ሕዝብ ታሪክ

የሚናገሩ፥ በብሉይ ኪዳን ሕጎች ላይ ማብራሪያ የሚሰጡና በስብከቱ ውስጥ ይናገራቸው የነበሩትና በመልዕክቱም ውስጥ የጻፋቸው ግጥሞች የሚገኙባቸው የግጥም መጻሕፍት ሳይሆኑ አይቀሩም። ጳውሎስ የፈለገው በሕይወት ዘመኑ መጨረሻ ላይ የነበሩትን ሳምንታት ወይም ወራት ውድ የሆኑትን መጻሕፍት ማጥናትና እስከ ዕድሜው መጨረሻም ተማሪ መሆንን ነበር።

በ1536 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በመሥዋዕትነት የተገደለ የአንድ እስረኛ ታሪክም ከዚህ ከጳውሎስ ታሪክ ጋር ይመሳሰላል። አንዳንድ ዕቃዎች እንዲላኩለት ለዋናው ገዢ የጻፈው ደብዳቤ በከፊል እንዲህ ይላል፡-

«ትንሽ ሙቀት የሚሰጥ ባርኔጣ፥ ሻማና ገንባሌዬን የምጠግንበት ለመጣፊያ የሚሆን እራፊ ጨርቅ ይላክልኝ። ጊዜዬን በጥናት እንዳሳልፍ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ፥ የዕብራይስጥ ቋንቋ የሰዋሰውና የመዝገበ ቃላት መጻሕፍቴ በቶሎ እንዲላኩልኝ እለምናለሁ።»

ጳውሎስና ይህ ሰው ሕይወታቸው በመሥዋዕትነት ከማለፉ በፊት የነበራቸውን ጊዜ ያሳለፉት የብራና መጻሕፍትን በማጥናት ነበር።

የመንፈሳዊ አገልጋይ ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በመመራት በትጋት የእግዚአብሔርን ቃል የሚያጠና መሆኑን ያለ ጥርጥር እንተማመናለን። አሁን እኛ የምናተኩረው ግን በተጨማሪ ስለሚያነባቸው ነገሮች ነው።

በመንፈስም ሆነ በአእምሮ ማደግ የሚፈልግ ሰው ጊዜውን የሚያሳልፈው ከመጻሕፍት ጋር ነው። ሙያው ፍሬያማና የተሳካ እንዲሆንለት የሚፈልግ የሕግ ባለሙያ በሕግ በኩል ከሚታዩት ለውጦች ጋር እኩል መራመድ አለበት። የሕክምና ባለሙያም በሕክምና መስክ ከሚደረጉት ለውጦች ጋር እኩል መራመድ አለበት። መንፈሳዊ አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃልና መመሪያዎች በሚገባ ማወቅ እንዳለበት ሁሉ የእርሱን መመሪያ በሚፈልጉት ሰዎች አእምሮ ውስጥ ምን እንደሚካሄድም ማወቅ ያስፈልገዋል። ይህንን ማድረግ እንዲችል ደግሞ የተለያዩና ምርጥ መጻሕፍትን ማንበብ ይኖርበታል። በጥበብና በዕውቀት የበለጸጉ መንፈሳዊና ጥንታዊ መጻሕፍትን የማንበብ ፍላጎት በዘመናችን እየደበዘዘ መጥቷል። በዓለም ታሪክ ውስጥ በየትኛውም ዘመን ከኖሩት ሰዎች ይልቅ በአሁኑ ዘመን ያሉት ሰዎች ትርፍ ጊዜ አላቸው፤ ብዙዎች ግን በፍፁም መጽሐፍ የሚያነቡበት ጊዜ እንደሌላቸው ይናገራሉ። መንፈሳዊ አገልጋይ ግን ጨርሶ ይህንን የመሰለ ምክንያት ሊሰጥ አይገባውም።

ጆን ወስሊ ከፍተኛ የማንበብ ፍላጎት ስለነበረው በየቀኑ በፈረስ ከ5090 ኪሎ ሜትሮች በሚጓዝበት ወቅት እንኳ መጽሐፉን ያነብብ ነበር። በዚሁም ወቅት በተለያዩ ርዕሶች የተጻፉ መጻሕፍት አንብቧል። እያሌ የሳይንስ፥ የሕክምና ወይም የታሪክ መጻሕፍት በፈረሱ ይዞ ይጓዝ ነበር። በዚህ አኳኋን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ መጻሕፍት አንብቧል። «ክርስቶስን መምሰል» «ቅዱስ አኗኗርና ሞት» እንዲሁም «ዋናው ጥሪ» የተባሉትን ሦስት መጻሕፍት በሚገባ ያጠናው በዚህ ጊዜ ነበር። ወጣት አገልጋዮችን «አንብቡ! አለዚያም አገልግሎታችሁን ተዉ» ብሎ ይመክራቸው ነበር።

ማንበብ ለብዙ ነገር ይጠቅማል። ሰውነትን ያዝናናል፥ መንፈስን ያድሳል፥ አዕምሮን ያበስላል። ስለዚህ በቀን ውስጥ ለግማሽ ሰዓት ያህል ማንበብ እጅግ ጠቃሚ ነው።

አንድ ምሁር በአንድ ሳምንታዊ ጋዜጣ ላይ ስለ መጻሕፍት ጥቅምና ጉዳት የሚከተለውን ሐተታ አቅርቦ ነበር፡- «በአሁኑ ዘመን የሚገኝ ክርስቲያን ጥንታዊ መጻሕፍትን ማንበብ

ከዓቅሙ በላይ አድርጎ የሚገምተው ለምንድን ነው? ትውልድ አሳልፎ አዲስ ትውልድ በተተካ ቁጥር የሰዎች የማስተዋልና የመረዳት ችሎታ ዝቅ እያለ ሲሄድ አልታየም። ከአባቶቻችን የምናንስበት ምንም ነገር የለም፤ አስፈላጊውን ጥረት የማድረግ ዝንባሌ ካለን እነርሱ ያሰቡትን እኛም ማሰብ እንችላለን። በአሁኑ ዘመን የሚጻፉት መንፈሳዊ መጻሕፍት ጥራት ዝቅተኛ ሊሆን የቻለው ከመንፈሳዊነት እንጂ ከትምህርት እጥረት አይደለም። ማንኛውንም ዓይነተኛ መንፈሳዊ መጽሐፍ ለመረዳት አንባቢው ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ሊቀድስና ብዙዎቹ ዘመናዊ ክርስቲያኖች ካላቸው አስተሳሰብ ሊለይ ያስፈልጋል። የቀድሞዎቹ ክርስቲያን አባቶቻችን የጻፏቸው መጻሕፍት ለማስተዋል አስቸጋሪ አይደሉም። እግዚአብሔርን የሚወዱ ሰዎች ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው ሊያነቧቸው ይችላሉ። « ... ሰዎች ጥንታዊ የክርስትና ጽሑፎች ለመረዳት ያልቻሉት በመጻሕፍቱ ውስጥ የታዘዙትን ትዕዛዛት ሊታዘዙ ፍላጎት ስለማይኖራቸው ነው።»

## ማንበብ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

ወደ ዕረፍት በሚሄድበት ወቅት ብዙ መጻሕፍት ያነብ የነበረ አንድ ሰው «መነቃቃትን ለማግኘት ማንበብ ያስፈልጋል» ብሏል።

መጽሐፍ መነበብ ያለበት ያዘለውን መልዕክት ለመቃወም ወይም ለመደገፍ መሆን የለበትም፤ በውስጡ ያለውን ቁም ነገር ለማመን ወይም ለወሬና ለንግግር የሚሆኑ ነጥቦችን ለመውሰድም መሆን የለበትም። መጽሐፍ መነበብ ያለበት የያዘውን መልዕክት መዝኖ ግምት ለመስጠትም ጭምር ነው። አንዳንድ መጻሕፍት መፈተን ይኖርባቸዋል። አንዳንዶች በቀጥታ ተቀባይነት ሊያገኙ ያስፈልጋል፤ አንዳንዶች ደግሞ ያዘሉት መልዕክት ተቀባይነት የሚያገኘው ከተገመገመ በኋላ ነው።

አንድ ጸሐፊ ደግሞ የግሉን አስተያየት ሲሰጥ «መጽሐፍ የምናነበው አዕምሯችንን መጋዘን ለማድረግ ወይም አስተዋይ፥ ምሁር እና ሌሎችን የምንበልጥ መስሎ ለመታየት ከሆነ ከሁሉ የከፋ ጥቅመቢስ የሆነ አመለካከት አለን ማለት ነው» ብሏል።

መንፈሳዊ አገልጋይ መጻሕፍትን ማንበብ የሚገባው የመንፈስ ተሐድሶ ለማግኘት መሆን አለበት፤ ይህ ዓላማው መንፈሳዊ አገልጋይ ማንበብ ከሚገባው መጻሕፍት ዓይነት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት አለው። ልብና አዕምሮን የሚነኩ ጽሑፎችን የሚያቀርቡ ጸሐፊዎች አሉ። አገልጋዮች ማንበብ የሚገባቸው መነቃቃትና መበረታታት የሚሰጡ መጻሕፍትን ነው።

መንፈሳዊ አገልጋዮች ሊያነቧቸው የሚገቡ መጻሕፍት አዕምሮን የሚያነቃቁና አዲስ ሃሳቦችን እንዲያፈልቁ የሚረዷቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

መንፈሳዊ አገልጋይ የስብከትና የማስተማር ችሎታዎቹን የሚኮተኩቱለትንና የሚያሳድጉለትን መጻሕፍት ማንበብ ያስፈልገዋል። ለዚህ ዓላማ ደግሞ የቃላት ዕውቀታችንን ለማስፋት ከሚረዱን ማሰብ እንድንችል ከሚያስተምሩን ተደማጭና ሰዎችን ወደ እምነት የሚያደርሱ ንግግሮችን ማድረግ ከሚያጎናፅፉን መጻሕፍት የበለጠ የሚረዳን የለም። የታሪክ መጻሕፍት ሰዎችን ጠቢብ ያደርጓቸዋል፤ የግጥም መጻሕፍት ደግሞ የማስተዋል ችሎታን ያዳብራሉ። የሒሳብ መጻሕፍት ጥበበኛና ብልሐተኛ ያደርጋሉ፤ የተፈጥሮ ፍልስፍና መጻሕፍትም የሰውን የመረዳት ችሎታ ጥልቀት ያለው እንዲሆን ይረዳሉ፤ የሥነ ምግባር

መጻሕፍት ቁምነገረኛ ያደርጋሉ! ውበት ባለው አነጋገር የተጻፉ መጻሕፍት በውይይት የማሳመን ችሎታ ያጎናጽፋሉ።

መንፈሳዊ አገልጋይ ስለ አንዳንድ ነገሮች መረጃ ሲሰበስብ መጻሕፍት ማንበብ ይኖርበታል። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በአሁኑ ወቅት የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ስለማናቸውም ነገር መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በቂ መረጃ ማግኘት የሚቻለው ከማንበብ ነው። መንፈሳዊ አገልጋይ ከዘመኑ ጋር አብሮ ለመራመድ ማንበብ ይኖርበታል፥ ስለተሠማራበት የሥራ መስክም በቂ ሃሳብ ሊኖረው ይገባል።

ከፍተኛ የአስተሳሰብ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ሃሳብ ለማግኘት ማንበብ አስፈላጊ ነው። በተለያዩ ዘመን የኖሩትን የታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ጽሑፎቻቸውን በማንበብ ነው።

ከአንድ መጽሐፍ የሚገኘውን ጥቅም መገመት አይቻልም። በሌላ በኩል ደግሞ ከመጥፎ መጻሕፍት የሚገኘውንም ጉዳት እንዲሁ መገመት የሚቻል አይደለም።

## መንፈሳዊ አገልጋይ ማንበብ የሚገባው ምንድን ነው

የአንድ ሰው ጸባይ የሚታወቀው ለጓደኝነት ከሚመርጣቸው ሰዎች ሕይወት ነው። ሰው የሚያነባቸው መጻሕፍትም እንዲሁ ባሕርዩን ያመለክታሉ። የሚያነባቸው መጻሕፍት የውስጣዊ ረሃቡና ጉጉቱ መግለጫ ናቸው። መግዛት ያለብን መጻሕፍት ከሁሉ ይልቅ ይጠቅሙናልና ተልዕኳችንን ለመፈጸም ይረዱናል የምንላቸው ሊሆኑ ይገባል። የምናነባቸው መጻሕፍት ከማንነታችን! ከምንሠራው ሥራና ለመሥራት ከምናቅደው ጋር ሰፊ ግንኙነት አላቸው።

መጻሕፍትን የሚወድ ሰው ለመጻሕፍት ያለው አመለካከት ለሰዎች ካለው አመለካከት ጋር ይቀራረባል። «የምወዳቸው» የሚላቸውን መጻሕፍት ወደ ምርኮ ቢሄድ እንኳ ይዟቸው ይሄዳል። ሌሎች ደግሞ ከዚህ በበለጠ መንገድ መጻሕፍትን እንደ ጓደኞቻቸው ይቆጥራሉ። ለእነርሱ ብርቅ የሆኑትን መጻሕፍት ደግሞ እንደ ወዳጆቻቸው ይቆጥሯቸዋል።

አንድ ጸሐፊ የግሉን አስተያየት ሲሰጥ «መጻሕፍትን ያለ ገደብ ከማንበብ ይልቅ ጥቂት መጻሕፍትን ጥርት ባለ ሁኔታ ማንበብ ይሻላል» ብሏል። አንድ ፈላስፋም የራሱን አስተያየት ሲሰጥ «እንደ ሌሎች ሰዎች እጅግ ብዙ መጻሕፍትን አንብቤ ብሆን ኖሮ የማውቀው ጥቂት ብቻ ይሆን ነበር» ብሏል።

የግጥም መጻሕፍትን ማንበብ ይወድ የነበረ አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ስለ ራሱ ምርጫ የሚከተለውን ጽፏል፦ «ጽሑፎቻቸው ከፍተኛ ሥነ ምግባራዊ ባሕርይና ስሜት የሚንፀባረቅባቸውን ግጥም ጸሐፊዎች እወዳቸዋለሁ። ... ያንዳንዶች ጽሑፍ አጋጣሚ ሁኔታዎችን ብሩህ ያደርጋል! ነገር ግን ከብርሃን ይልቅ ስሜትን የሚያንቀሳቅስ ጽሑፍ እወዳለሁ። የአንዳንድ ጸሐፊዎች አዕምሮ እንደ ምላጭ ነው! ስሜትና ሙቀት የሌለው ብርሃን ነው። ብዙ ዘማሪያን ግሩም ግጥሞች ይቀኛሉ! ነገር ግን ስሜቶቼን አያነሣሡም! ግሩም ዘማሪዎች ቢሆኑም እንኳ ቃላት ያበዛሉ። በቅድስና ውበትና በውበት መሃከል ገደብ የለሽ ልዩነት አለ! አንደኛው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ባሕርይ ሲያመራ ሌላኛው ደግሞ ሰውን በመጥፎ የስሜት ረግረግ ውስጥ ያሰጥመዋል።»

ሌላ ምሁር ደግሞ «የሰዎችን የሕይወት ታሪክ የሚያወሱ መጻሕፍት ማንበብ ያስፈልጋል» የሚል አስተያየት ሰንዝሯል። አንድ ሰው መንፈሱ ሳይነሣሣና ጉጉት ሳይኖረው ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ሰዎች የሕይወት ታሪክ መጻሕፍት አያነብም። የታላላቅ ሰዎች ሕይወት እኛም ሕይወታችንን የጋለ ማድረግ እንደሚገባን ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። የታላላቅ ሰዎች የሕይወት ታሪክ መጻሕፍት ሌሎችን ምን ያህል ለከፍተኛ ተልዕኮ ሊቀሰቅሱ እንደሚችሉ ማንም በቀላሉ ሊገምት አይችልም።

በስብከት ችሎታውና በማስተማር ዘዴው ታዋቂ የነበረ አንድ ሰባኪ የታላላቅ ሰዎች የሕይወት ታሪክ መጻሕፍትን ጠቃሚነት አዘውትሮ ይናገር ነበር። እነዚህን መጻሕፍት ማንበብ ከክርስትና ትምህርት አንዱ ክፍል ነው። ክርስቲያን በአገልግሎቱ ሊጠቀምባቸው የሚገቡ አያሌ ምሳሌዎችን አዝለዋል። እነዚህ መጻሕፍት ክርስቲያን የመልካም ባሕርያትን እውነተኛ ዋጋ እንዲያውቅ፥ ለራሱ ሕይወት ግብ እንዲኖረው፥ የመጨረሻ ዓላማው ላይ መድረስ ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን እንዲረዳና አስፈላጊ ያልሆኑ ጉጉቶችን ለማስወገድ እንዴት ራስን መካድ እንደሚያስፈልግ እንዲገነዘብ ይረዱታል። እንዲሁም እግዚአብሔር ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ራሳቸውን በሰጡት ሰዎች ምን ያህል እንደሚጠቀም እንዲያውቅም ይረዱታል።

የሚከተሉት ሰዎች ከማንበብ በሚያገኙት እርካታ አገልጋዩ መርካት የለበትም። አገልጋይ ማንበብ ያለበት ቀላል የሆኑ መጻሕፍትን ወይም ከእርሱ ሙያ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ብቻ መሆን አይኖርበትም።

ከችሎታችን በላይ የሆኑትን ነገሮች ለመሥራት መሞከር የተሻለ ነው። ከእኛ ሃሳብ ጋር የሚስማሙ ሰዎች የጻፉቸውን ጽሑፎች ብቻ ሳይሆን ሃሳብ ለሃሳብ ልንለዋወጥ ከምንፈልጋቸው ከኛ ሃሳብ ለየት ያሉትንም ማንበብ ያስፈልገናል። ከሃሳባችን ጋር የማይስማማውን ጽሑፍ ከማንበባችን በፊት ማውገዝ አይገባንም። የእነርሱ ቁምነገር እውነትን እንድንመረምርና አመለካከታቸውንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንድናገናዝብ ይረዳናል። ሌሎች ሰዎች ስለነዚህ መጻሕፍት ባሰፈሩት ሃሳብ ወይም ባወጡት አቃቂር መርካት የለብንም። እነዚህን መጻሕፍት አናነብም በማለት በራሳችን ላይ ችግር መፍጠር አያስፈልግም። አዳዲስ ሃሳቦችን መፍራት መልካም አይደለም፤ ደግሞም በአዳዲስ ሃሳቦችም መወሰድ አይገባም።

ስለዚህ መንፈሳዊ አገልጋይ አገልግሎቱንና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለውን የታማኝነት ተግባር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ መጻሕፍት ማንበብ ይኖርበታል።

## መንፈሳዊ አገልጋይ መጻሕፍት

## ማንበብ ያለበት እንዴት ነው?

በአንድ ገጽታው ማንበብ ከጽሑፎች ትምህርት ማግኘት ነው። ማንበብ የሚፈልገው ጽሑፎችን መመልከት ብቻ አይደለም፤ ጽሑፎቹ ያዘሉትን ሃሳብ ማሰላሰልንም ይጠይቃል። ማንበብ ቀላል ነው፤ የንባብን ፍሬ በአዕምሮ ውስጥ ማስቀመጥ ግን እጅግ አዳጋች ነው። ታዲያ ማንበባችን ፍሬ ካላስገኘ ጥቅሙ ምንድን ነው?

አንድ የግጥም ጸሐፊ ለአንዲት መንፈሳዊ ባልቴት፦ «በምታጠብበት ወቅት ሰዋሰው አጠናለሁ፤ ልብሴን እየለበስሁ ታሪክ አነባለሁ፤ ቁርሴን እየበላሁ ጋዜጣ እመለከታለሁ፤ በቀን

ውስጥ የማልማርበት ደቂቃ የለም» ብሎ ቢነግራት እርሷም ትኩር ብላ ተመልክታው «ታዲያ ሃሳብህን የምታገለባብጠው በምን ሰዓት ነው?» በማለት ጠይቃዋለች። ሃሳብን ሳይሰበስቡ ማንበብ ይቻላል። ሃሳባችን ሳይሰበሰብ ከምናነበው ንባብ ምንም ጥቅም አናገኝበትም።

አንድ መንፈሳዊ ምሁር መጽሐፍ ስለ ማንበብ ለተማሪዎቹ የሚከተለውን ምክር ሰጣቸው:-

«ያሏችሁ መጻሕፍት ያዘሉትን መልዕክት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራችሁ ሥር አድርጉ። ደጋግማችሁ አንብቧቸው፤ አሰላስሏቸው። ወደ ውስጠኛው ሰውነታችሁ ዘልቀው ይግቡ። አንድ ጥሩ መጽሐፍ ደጋግማችሁ ካነበባችሁት በኋላ ያዘለውን መልዕክት በማስታወሻ ለመያዝና ትንተና ለመስጠት ሞክሩ። አንድ ተማሪ ላይ ላዩን ካነበባቸው ሃያ መጻሕፍት ይልቅ ደህና አድርጎ አንብቦ በተረዳው አንድ መጽሐፍ አስተሳሰቡን ሊለውጥ ይችላል። በችኮላ ማንበብ የአነስተኛ ትምህርት ምክንያት ሲሆን ኩራትን ያስከትላል። ብዙ ሰዎች ሃሳበ ስንኩል ሆነው የቀሩት ብዙ መጻሕፍትን ለማንበብ ሲሉ ማሰላሰል በጎደለው ሁኔታ በችኮላ ስለሚያነቡ ነው። ዘወትር የንባባችሁ ዓላማ ብዙ መጻሕፍትን ከማንበብ ይልቅ ከአንድ መጽሐፍ ብዙ ቁምነገሮች ማትረፍ ይሁን።»

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን መመሪያዎች በተግባር ብንተረጉማቸው ንባባችን ይበልጥ ትርጉም የሚሰጥና ጠቃሚ ይሆናል።

1. ጊዜን ለማሳለፍ ብቻ መጽሐፍ ማንበብ ጥሩ ልማድ አይደለም። ጓደኞቻችሁን እንደምትመርጡ ሁሉ መጻሕፎቻችሁንም ምረጡ።

2. ስታነቡ እርሳስና ማስታወሻ ደብተር ያዙ። አንዳንድ ጊዜ አዕምሮ የማስታወስ ችሎታውን ሊያጣ ስለሚችል ብዙ ማንበብ ጊዜ ማባከን ነው። ስለዚህ የማስታወሻ አያያዝ ዘዴ ይኑራችሁ። በጥቂት ጊዜያት ውስጥም ይህ ዘዴ ምን ያህል ፍሬያማ እንደሆነ ትረዳላችሁ።

3. ከመጻሕፍት የምታገኟቸውን ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች የምትመዘግቡበት ደብተር ይኑራችሁ። በዚህ ውስጥ የግላችሁንም አስተያየቶች ጨምራችሁ መመዝገብ ትችላላችሁ። በዚህ መንገድ ለወደፊቱም እንዲጠቅማችሁ ሊጠፋ በማይችል ሁኔታ ቅርስ ታኖራላችሁ።

4. በተቻለ መጠን ታሪካዊና ሳይንሳዊ እንደዚሁም ሌሎች ዘገባዎች እውነተኛ መሆናቸውን አረጋግጡ። የማታውቋቸውን ቃላት ትርጉም ሳትረዱ አትለፉ።

5. የምታነቧቸውን መጻሕፍት ዓይነት ለዋውጡ፤ ለውጥ ለሥጋ ዕረፍት እንደሆነ ሁሉ ለአዕምሮም ዕረፍት ነው።

6. የምታነቧቸው መጻሕፍት እርስ በእርሳቸው የሚገናዘቡና የሚመሰካከሩ ይሁኑ። አንዱ መጽሐፍ ከሌላው መጽሐፍ የምታገኙትን የሚደግፍና የሚያሰፋ ይሆናል።

ማንኛውም መጽሐፍ በሦስት ዓይነት መንገዶች መነበብ ይኖርበታል። የመጀመሪያው ንባብ ፈጣንና ሳያቋርጥ የሚቀጥል መሆን አለበት። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ቁምነገሮች በከፊል የሚያውቀው አዕምሯችን በዚህን ጊዜ የመጽሐፉን ሃሳብ አስቀድሞ ካለን ዕውቀት ጋር ያገናዝበዋል። ከዚያ በኋላ ያነበብነውን መጽሐፍ ለዕውቀታችን ምን ዓይነት አስተዋጽዖ እንዳበረከተ የምንመረምርበት ጊዜ እንዲኖረን ያስፈልጋል። ሁለተኛው ንባባችን ጥንቃቄ የተሞላው ዝግ ያለና የተብራራ ገለጻ ለማግኘት የሚደረግ መሆን ይኖርበታል። እያንዳንዷን

ነጥብ ትኩረት በመስጠት ማሰላሰልና ለወደፊት በሚጠቅም ሁኔታ ማስታወሻ መያዝ አስፈላጊ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሦስተኛውን ዙር ንባብ መጀመር እንችላለን። ይህ ንባብ በመጠኑም ቢሆን ፈጣንና የማያቋርጥ መሆን ይገባዋል፤ በዚህ ወቅት ስለመጽሐፉ ያለንን አስተያየት ገጾቹን እየጠቀስን ከመጽሐፉ ጀርባ ልንጽፍ እንችላለን።

በስኮትላንድ ውስጥ ይኖር የነበረ አንድ የእግዚአብሔር አገልጋይ ቁጥራቸው እስከ አሥራ ሰባት ሺህ የሚደርስ መጻሕፍት ነበሩት። የዚህ አገልጋይ ልጅ ስለ አባቱና ስለነበሩት መጻሕፍት ሲናገር «አባቴ ስብከቶቹን በጥንቃቄ ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ ቢያጠፋም ስብከቶቹ እምብዛም ያነበባቸውን መጻሕፍት አላንፀባረቁም» ብሏል።

ትልቁ አደገኛ ችግር የሚፈጠረው በዚህ ወቅት ነው። መጻሕፍት ሃሳቦች ከአንዱ ሰው አዕምሮ ወደ ሌላው የሚተላለፉበት መንገድ ናቸው። የዚህ አገልጋይ መንፈሳዊ ሕይወት ከመጻሕፍት ጋር ግንኙነት ነበረው፤ ያገለግላቸው የነበሩት ሰዎች ግን ከእርሱ ማንበብ ምንም ጥቅም ሊያገኙ አልቻሉም። ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙ መንፈሳዊ አገልጋይ በሚናገራቸውና በሚጽፋቸው ቃምነገሮችና በሚያነባቸው መጻሕፍት መሃከል ግንኙነት መመሥረት ተግባሩ ነው።

በአውስትራሊያ ይኖር የነበረ በጣም መጻሕፍት ማንበብ የሚወድ አንድ አገልጋይ በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈሳዊ ትምህርት የቤተ ክርስቲያኑን አባላት ዕውቀት ሊያሳድግ አሰበ። ቀስ በቀስም ለመጻሕፍት ያለውን ፍቅር ለቤተ ክርስቲያን አባላት መግለፅ ጀመረ። እያደሩም ምዕመናን ጥልቀት ያላቸውን መጻሕፍት በማንበብ ደስ ተሰኙ። ከዚህም የተነሣ በአካባቢው የነበሩ ገበሬዎች ለወንጌል አገልግሎት አመቺ የሆነ መጻሕፍት ቤት መሠረቱ። ተመሳሳይ ዓላማ ቢኖራቸው ኖሮ ሌሎችም አገልጋዮች ለመንፈሳዊ መጻሕፍት ያላቸውን አድናቆት ለምዕመናን በመግለጽ አንባቢ ወደ መሆን በመሯቸው ነበር።

# ምዕራፍ 13

## አገልጋይነት የሚያስከፍለው ዋጋ

«እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ እኔ የምጠመቀውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?» ማር.10:38።

አብረውት የሚኖሩ ሰዎች ሊከፍሉት ከሚፈልጉት ዋጋ የበለጠ ዋጋ ለመክፈል ያልተዘጋጀ ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ አገልጋይ የመሆን ፍላጎት ሊኖረው አይገባም። እውነተኛ አገልግሎት ምንጊዜም አገልጋዩን ሁለንተናውን እንዲከፍል ይጠይቃል፤ አገልጋይ ይበልጥ ፍሬያማ እንዲሆን ከፍተኛ ዋጋ መክፈል አለበት።

በለንደን ከተማ የሚገኘውን የፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት የመሠረተው ኩዊንተን ሆግ የተባለው ሰው ድርጅቱን ለመመሥረት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ያንን የሚያህል ትልቅ ድርጅት ለመመሥረት ምን ያህል ዋጋ እንደከፈለ ሲጠየቅ «ብዙም አይደለም፤ በቀላሉ የአንድ ሰው ደም ነው» የሚል መልስ ሰጥቷል። እያንዳንዱ ከፍተኛ ክንዋኔም የሚጠይቀው ይህንን

ዋጋ ነው፤ በአንዴ ተቆጥሮ የሚከፈል ገንዘብ አይደለም። በየጊዜው የምንከፍለው ነገር አለ፤ በየቀኑ ክፍያውን ማስቀመጥ አለብን። በየጊዜው አዳዲስ ጥያቄዎች ይቀርባሉ፤ አገልጋዩ መክፈሉን ካቆመ የአገልግሎቱ ሥልጣን እየቀነሰ ይሄዳል። ሌሎችን የማዳን ፍላጎት ካለን ራሳችንን ልናድን እንደማንችል ጌታችን አበክሮ አስተምሯል።

መንፈሳዊ ኃይል የሚፈልቀው ከመንፈሳዊ ሕይወት ነው፤ ይኸውም በዙፋኑ ላይ ካለው ከእግዚአብሔር ተነሥቶ ወደ ሰዎች ይፈሳል ማለት ነው። ስለዚህ አገልጋይ ለመሆን የሚሹ ሰዎች ዋጋውን መክፈል አለባቸው። ይህንንም ደግሞ ሊያገኙ የሚችሉት ከእግዚአብሔር ብቻ ነው።

## ራስን መሥዋዕት ማድረግ

ይህ በየቀኑ ሊከፈል ከሚገባው ነገር አንዱ ነው። በመንፈሳዊ አገልግሎት ጎዳና ላይ መስቀል ተተክሏል፤ አገልጋይ በዚህ መስቀል ላይ ለመሰቀል የተስማማ ሰው መሆን ይኖርበታል። መለኮታዊ ጥሪ አያሻማም። «እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷል ... እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል» 1ዮሐ.3፡16። የክርስቶስ መስቀል በውስጣችን እንዲሠራ በምንፈቅድበት መጠን የክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት ምን ያህል በእኛ አማካይነት የሚገለጽ የመሆኑ መመዘኛ ነው። ሞቱ በእኛ ሕይወቱ በእናንተ ይሠራል። መስቀሉን መሸሽ አገልግሎትን ማጣት ነው።

«ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» ማር.10፡44-45። በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ታሪካቸው የተዘረዘረው የእምነት ጀግኖች በሙሉ ለአገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለመሥዋዕትነትም ጭምር የተጠሩ ነበሩ። እግዚአብሔር በሥራው ውስጥ ለመሪነት የሚፈልጋቸው ሰዎች ልዩ ባሕርይ የራስን ምርጫ ለመተው ፈቃደኛ መሆንና ለእግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ ፍላጎትን ሁሉ መተው ነው። በአንድ የመኪና ሞተር መጠገኛ ጣቢያ «መኪናዎቻችሁ ሥር ተኝተን ጥገና በማካሄድ ከሌሎች መሠሎቻችን ሁሉ የበለጠ እንቆሸሻለን» የሚል ማስታወቂያ ነበረ። እናንተ መኪና ቢኖራችሁ ደምበኛ የምታደርጉት እንዲህ ዓይነቱን ጋራዥ አይደለም?

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለሰዎች ማሳየት የፈለገው ቁስሉን ብቻ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ በኤማሁስ መንገድ ይጓዙ በነበሩበት ወቅት ኢየሱስን ወይም መልዕክቶቹን ለይተው ማወቅ አልተቻላቸውም። ዳቦ ቆርሶ እስኪሰጣቸውና በእጁ ላይ ቁስሉን እስኪያዩ ድረስ እርሱን ለመረዳት የነበራቸው ስሜት በፍጹም አልተቀሰቀሰም ነበር። ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ተስፋ ቆርጠው በነበሩት ደቀ መዛሙርቱ መሃከል ተገኝቶ ያሳያቸው እጆቹንና ጎኑን ነበር። ቁስል የታማኝ ደቀ መዝሙርነትና የእውነተኛ አገልግሎት ምልክት ነው። ሕይወቱ በሥቃይ ያለፈች አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ፡- «በከፍተኛ ሥቃይ ነፍሱ ያለፈች የመጀመሪያዎቹ ሰማዕታት ወገን ነው» ተብሎ ተነግሮለታል። በምስማር የቆሰሉት ቁስሎቹና በጦር የተወጋው ጎኑን ያህል የሰዎችን ስሜት የሚነካ ምንም ነገር የለም። ጳውሎስ ደህና አድርጎ በተረዳው መሠረት እነዚህ የታማኝነት መለኪያዎች ናቸው። «እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜያለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድስንኳ አያድክመኝ» ገላ.6፡17።

ጳውሎስ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚጠይቀውን ዋጋ ሊከፍል ፈቃደኛ መሆኑ በ2ቆሮ.4፡8-11 ተብራርቷል።

# ያለ ድጋፍ መቆም

መንፈሳዊ አገልጋይ መሆን ብቸኛ የመሆን ዕጣ ነው። አገልጋይ ዘወትር ተከታዮቹን ቀድሞ መገኘት ያስፈልገዋል። የሰዎች ሁሉ ጓደኛ መሆን ቢገባውም በብቸኝነት ሊጓዛቸው የሚገቡ ጎዳናዎችም አሉ። የኃላፊነትን ሸክም ተቀብሎ መሥራት የነበረበት አንድ ሰው ሲናገር፡- «አሁን ከእግዚአብሔር በቀር ከእኔ ጋራ ማንም የለም» ብሏል። ወዳጆቹን ሁሉ ትቶ መሄድ ወደነበረበት የሥራ ቦታ በሚጓዝበት ወቅት ሁሉን ትቶ እንደመጣና ብቻውን እንደሆነ አስተውሏል፤ ከአምላኩም ጋር ቆሟል።

ሰዎች በተፈጥሯቸው አብሯቸው የሚሆን ጓደኛ የመፈለግ ዝንባሌ አላቸው፤ የኃላፊነትን ቀንበር ከሌሎች ጋር አብሮ ለመሸከም መፈለግም ሌላው የሰዎች ፍላጎት ነው። አብረው በሚሠሩ ሠራተኞችና ጓደኞች ላይ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ወይም ብዙ ውጤቶች የሚያስከትል ውሳኔ መስጠት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ልብን የሚሰብር ነው፤ እነርሱን ብቸኛ ማድረግም ከዚህ ተለይቶ አይታይም። ይህ አገልጋይ ሊከፍላቸው ከሚገቡ ታላላቅ ዋጋዎች አንዱ ነው፤ ቢሆንም ይህ ዋጋ የግድ መከፈል አለበት። ሙሴ መሪ ሲሆን ይህንን ዋጋ ከፍሏል፤ ከተፈጠረው አለመግባባት፥ ከተሰነዘረበት ነቀፋና በሥልጣን ትባልጋለህ ተብሎ ከቀረበበት ወቀሳ የተነሣ ብቸኝነት ተሰምቶታል። ዘመናችን ከሙሴ ዘመን የተለየ አይደለም።

ነቢያት ከሰው ሁሉ ይልቅ ብቸኞች ነበሩ። ኖኅ በጥፋት ውስጥ ለነበሩ ሰዎች ስለሚመጣባቸው ፍርድ እየተናገረ ኖሯል፤ ለብቸኝነቱ ካሣ የሆነው ግን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑ ነበረ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በነበሩባት ከተማ ውስጥ ሊፈጸም ተቃርቦና ወዲያውኑ ንስሐ በመግባት ሊለወጥ ይችል ስለነበረው ፍርድ መናገር የነበረበትን ዮናስን ያህል በብቸኝነት የተንገላታ ማንም አልነበረም። በአሁኑም ዘመን በአርቀ አስተዋይነቱ የወደፊቱን ተመልክቶና የዘመኑን ባሕርይ ተቃርኖ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተላልፍ ወንጌላዊ ብቸኛ ይሆናል።

ከሰዎች ጋር ተዋዶ የመኖር ፍላጎት የነበረው ጳውሎስ በዘመኑ በነበሩት ሰዎች ተቀባይነትና ተሰሚነት በማጣት መራራ ችግር የቀመሰ ሰው ነው፤ ጠላቶቹ እርሱ ያልሆነውን ነው እያሉ ያስወሩበት ነበር፤ ወዳጆቹም ይከዱት ነበረ። «በእስያ ያሉቱ ሁሉ ከእኔ ፈቀቅ እንዳሉ ታውቃለህ» በማለት በ2ጢሞ.1፡15 የተናገረው ቃል ምን ያህል የጢሞቴዎስን አንጀት ደብላው ይሆን!

በዓለም ላይ ከኖሩት ታላላቅ ሰዎች ብዙዎቹ ብቸኞች ነበሩ። ቅዱስ መሆን የሚፈልግ ሰው ለመቀደስ መክፈል ያለበት ዋጋ ብቸኝነት ነው። መንፈሳዊ አገልጋይ በወዳጅነት ሊቀርቡት የሚፈልጉትን ሰዎች ጓደኝነት መቀበል ያለበት ሰው ቢሆንም ኃላፊነቱንና ግዴታውን ለመወጣት ኃይለኛ ተቃውሞ እንዲጋፈጥ ሲገደድ ብቻውን ሊቆም ብቁ መሆን ያስፈልገዋል። ሁኔታዎች በሚያስገድዱት ጊዜ ከእግዚአብሔር በቀር ከሰው ሁሉ ተለይቶ ሊኖር ዝግጁ መሆን አለበት። «ሥራዬን እስካከናውን ድረስ የምታበረታታኝ እኅት ወይም ሴት ልጅ ሳትኖረኝ፥ አባት ወይም ወንድ ልጅ ሳይኖረኝ በምድር ብቸኛ በባሕርም ላይ ቤት የለሽ ሆኜ በትዕግሥት አልፋለሁኝ» ማለት የሚችል ሰው መሆን ይኖርበታል።

## ድካም

ዓለምን የሚያንቀሳቅሱ ሰዎች እስኪዝሉ ድረስ ሠርተው የሚደክሙ ናቸው። ይህ አነጋገር ምንም እንኳ ተቃውሞ ሊገጥመው የሚችል ቢሆንም ከሞላ ጎደል እውነት ያዘለ ነው። እያደር ቁጥራቸው የሚጨምረው አገልጋይን ፊት ለፊት የሚጋፈጡት ጉዳዮች አዕምሮውን አላሽቀው ጤናማ የሆነውን አቋሙን ያዳክሙታል። መንፈሳዊ አገልጋይ ግን ከዚህ እርጅና ለመታደስ ወዴት መሄድ እንዳለበት ያውቃል። ጳውሎስ ይህንን ምስጢር በሚገባ የተረዳ ሰው ነበር። «ስለዚህም አንታክትም፤ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል» ብሎ የተናገረው ለዚህ ነው፤ 2ቆሮ.4፡15-16። ኢየሱስ ከአገልግሎት የተነሣ ደክሞ ስለነበረ በውኃው ጉድጓድ አጠገብ አርፏል፤ ዮሐ.4፡6። የእርሱን እርዳታ ትፈልግ የነበረችው ሴትዮ በእምነት የልብሱን ጫፍ ስትነካ ኃይል ከእርሱ መውጣቱን ኢየሱስ አውቋል፤ ማር.5፡30። ከአንድ ሰው ኃይል ሳይወጣና የአስተሳሰብ ችሎታው በተግባር ላይ ሳይውል ምንም መልካም ውጤት ያለው ሥራ አይከናወንም።

ስጡኝ ባይ ሰው ለአገልግሎት አይበቃም። መንፈሳዊ አገልጋይ በዘመኑ ከሚኖሩት ሰዎች ይልቅ በበለጠ መሥራትና በትጋት ማጥናት እንዲችል በማለዳ ከመኝታው ሊነሣ ፈቃደኛ ካልሆነ ሰዎችን የመማረክ ችሎታ አይኖረውም። በቶሎ መጠገን የሚችል ልዩ አቋም ከሌለውና ለአገልግሎቱ ለመድከም ፈቃደኛ ካልሆነ መልካም ውጤት አይኖረውም። በጥበብ የተሞላ ሰው ዝለቱን ሊያስወግድና ሊዝናና በማናቸውም አጋጣሚ ሊጠቀም ይችላል፤ ይህ ካልሆነ ግን ጠቃሚነቱና አገልግሎቱ ይወሰናል።

በግብፅ ያገለግል የነበረ አንድ አገልጋይ ለበላይ መሥሪያ ቤቱ ጸሐፊ የጻፈው ደብዳቤ የሚከተለው ሃሳብ ሠፍሮበት ነበር፡- «በጣም ደክሚያለሁኝ፤ ይህንን የምጽፈው መሥራት እስኪያቅተኝ ስለደከምኩኝ ብቻ ነው፤ የድካሜ ብዛት እንቅልፌን አርቆታል። በልጅነቴ አርጅቻለሁ። የተለያዩ ሰዎችና ሐኪሞችም ጭምር ውጥረቴ ካልተቃለለ በቀር ዕድሜዬ እንደሚያጥር ነግረውኛል። ባለቤቴ ከእኔ ይበልጥ ተጨንቃለች። ፍጹም ዕረፍት ትፈልጋለች። የአገሬ ቤተ ክርስቲያን ምነው በዚህ ስላለው የሥራ ዕድል ብትገነዘብ! ይህንን ጥሪ የሚሰማ ማንም ሰው የለም? እባካችሁ እኛን ለመርዳት የተቻላችሁን ያህል አድርጉ።»

በዘመናቸው ባለው የመሥራት አጋጣሚ ለመጠቀም የሚፈልጉ አገልጋዮች እስኪደክሙ በመሥራት ይህንን ዓይነቱን ዋጋ ሊከፍሉ ፈቃደኞች ነበሩ።

በሃያ ዘጠኝ ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ አንድ አገልጋይ መሞቻው ተቃርቦ በነበረበት ወቅት ወደ አንድ የሥራ ጓደኛው ቀረበና «እግዚአብሔር ልናገረው የሚገባኝ መልዕክትና የምጋልብበት ፈረስ ሰጥቶኝ ነበር፤ አሁን ምን ላድርግ? ፈረሱን ገድዬዋለሁ፤ መልዕክቱን ማድረስ አልችልም» ብሎ ቅጥ ባጣ ሕይወት በመኖሩ አዝኖ ነግሮታል። የምንጠቀምበትን መጣሪያ ያለጊዜው ከጥቅም ውጭ ማድረግ ተገቢ አይደለም።

## ነቀፌታ

ማንኛውም አገልጋይ ከነቀፌታ ንጹሕ ሊሆን አይችልም። ከማናቸውም ነገሮች ይልቅ ትሕትናው በግልጽ ሊታይ የሚችለው ነቀፌታ በሚሰነዘርበት ወቅት ነው።

አንድ ክርስቲያን ለአንድ ወጣት አገልጋይ በጻፈው ደብዳቤ እንዲህ ብሎታል፦ «ስሙን ልጠቅሰው የማልፈልገውና እኔና አንተ ግን የምናውቀው ግለሰብ የሰነዘረብህን መራራ ነቀፌታ ከመቻልህ የተነሣ በረከት ማግኘትህን ሰምቼ ተደስቻለሁ። እኔንና ባለቤቴን በጣም የረዳን የሚደርስብን ነቀፌታ ሳይሆን ለእርሱ የምንሰጠው አጸፋ ነው። የበለጠ ነቀፌታ ይመጣል ብለህ በተስፋ መጠበቅ ያለብህ ይመስለኛል። ኃላፊነትህ እየጨመረ ሲሄድ ይህ የማይቀር ነገር ነው። ይህ ዓይነት ነቀፌታ ሰውን በትሕትና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲራመድ ያደርገዋል፤ እግዚአብሔርም እንደሚፈቅድ ይሠራል።»

ከፍተኛ ተቃውሞ ደርሶበት የነበረ አንድ አገልጋይ የነቀፈውን ሳይነቅፍና ራሱን ሳያመጻድቅ ተቃዋሚውን «ስለ ገሠጽከኝ ከልቤ በጣም አመሰግንሃለሁ፤ ይገባኛል፤ ግን በጸሎትህ እንድታስበኝ እጠይቅሃለሁ» የሚል መልስ ሰጥቶታል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ስለ ግል የክርስትና ሕይወቱ የከፋ ተቃውሞ ገጥሞታል። በዚህ ጊዜም «ስለሰጠኸኝ ትችት በጣም አመሰግንሃለሁ፤ ትችትህ ራሴን እንድመረምርና እንድጸልይ ያደርገኛል፤ ለልቤ ቅድስናም በኢየሱስ ላይ ወደ መታመን ያመራኛል፤ ከእርሱም ጋር የበለጠ ጣዕም ያለው ኅብረት እንዲኖረኝ ያደርገኛል» የሚል መልስ ሰጥቷል።

ይህ ዓይነት አመለካከት ያለው ሰው የሚሠነዘርበትን ነቀፌታ ከእርግማን ወደ በረከት፥ ከዕዳ መግባት ወደ ነፃ መውጣት ይለውጠዋል።

## ተቀባይነት ማጣት

መንፈሳዊ ሕይወቱን በትክክል ጠብቆ የሚራመድ አገልጋይ የመሪዎች አለቃ የሆነው ክርስቶስ በሄደበት መንገድ መሄዱ የማይቀር ነው። «ወደ ወገኖቹ መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም።» መሪዎች ሁሉ የተጠሉ ይሆናሉ ማለት አይደለም፤ ብዙዎች ግን ይህንን ሊቀምሱ ተገድደው ነበር።

ምዕመናን መልዕክቱን ባለመቀበል የሚያስቸግሩት አንድ አገልጋይ ነበረ። መንጋውን ወደ ለመለመ መስክና ውኃ ወደሚገኝበት ሥፍራ ማሰማራት ይፈልጋል፤ እነርሱ ግን ከቶውንም ለመመራት አይፈልጉም ነበር። የቤተ ክርስቲያኑም መዘምራን ክፉ ድርጊቶች ይፈጽሙበት ነበር።

ይህ አገልጋይ ችግሩን ሊቋቋመው ስላልቻለ መዘምራኑ በሙሉ ሥራ እንዲያቆሙ ጠየቀ። መዘምራኑ ሥራቸውን ከማቆማቸውም በላይ በተከታዩ እሑድ ጉባኤውንም መዝሙር እንዳይዘምር ለማሳደም ተነሡ። ከዚህ የተነሣ መዝሙር በሚዘመርበት ጊዜ ይህ አገልጋይ ብቻውን ዘማሪ ሆኖ ቀረበ፤ ግራም ተጋባ። በዚህ አገልጋይ ግራ መጋባት መዘምራኑና ጉባኤው ደስ ተሰኙ። ይህ ሁኔታ ለጥቂት ጊዜያት ቀጠለ። አገልጋዩም ከተፈጸመበት አድማ የተነሣ አዘነ፤ ብዙም ተጨነቀ።

ምን ማድረግ እንዳለበት ሊያውቅ ባልቻለበት ወቅት እግዚአብሔር ተናገረው። በአንድ የመናፈሻ ቦታ ተቀምጦ ሳለ አጠገቡ የጋዜጣ ቅዳጅ መሬት ወድቆ ተመለከተ። ይህም የጋዜጣ ቅዳጅ፦ «ማንም ሰው ከፍተኛ ተቃውሞ ሳይደርስበት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም» የሚል ከእርሱ ሕይወት ጋር የሚስማማ መልዕክት ነበረበት።

ከዚህ የበለጠ ምንም አልፈለገም። ለክርስቶስ ሲል ተጠልቷል፤ ይህንን እውነት ማወቁ ከፍተኛ ፍሬያማ አገልግሎት መስጠት ለመጀመር መግቢያ ሆነለት። ሰዎች ቢቃወሙትና ባይቀበሉትም በእግዚአብሔር ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ነበረው።

ከእግዚአብሔር ግልጽ የሆነ ጥሪ የሰማ አንድ ሌላ የቤተ ክርስቲያን እረኛ የመጋቢነት ሥራውን በፈቃዱ ለቀቀ፤ በዚህም ወቅት ማጣት፥ መናቅና በሰዎች መጠላት ምን እንደሆነ ተማረ። ይህ ሰው በታላቅ ከተማ ውስጥ የሚኖር መጋቢ ነበር፤ ሥራውንና በዓመት የሚያገኘውን የአምስት ሺህ ብር ደመወዝ በፈቃደኝነት ተወ፤ ያገለግልባት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላቀደው አዲስ ሥራ ማካሄጃ ዕርዳታ ከለከለችው፤ እርሱም ምንም ገንዘብ በማይገኝበትና አንድም ተከታይ በሌለበት ሥፍራ የብዙ ቤተሰብ አስተዳዳሪ ሆኖና አብረውት ያገለግሉ የነበሩት ብዙ ጓደኞቹ «አዲሱ ዕቅድህ አንተ በምትለው ቦታ አይሳካልህም» ባሉት ከተማ ተገኘ። ቸርነታቸውን ይለግሡኛል ያላቸው ሰዎች እንኳ ሊረዱት እንቢ ስላሉትና ፊት ስለነሡት ሕይወት ከሌላቸው ድንጋዮች ዕርዳታ ለማግኘት ተመኝቶ ነበር።

ወጣ ገባ የሆነውን ተቃውሞ የሞላበት መንገድ ያለፈው በማማረር ሳይሆን በደስተኝነት ነበረ። ይህ አገልጋይ ከደረሰበት ችግር የተነሣ የሚጓዘው በእሳትና በውኃ ውስጥ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር እርሱን ወደ ብልጽግና ለማምጣት ያዘጋጀው ጎዳና መሆኑን ተረድቷል።

ይህ አገልጋይ በእርግጥም የደረሰው ከብልጽግና ደረጃ ላይ ነበር። ይህ አገልጋይ ሳይሞት በፊት አምስት የወንጌል መልዕክተኞች ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶችን ሊያቋቁምና ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የወንጌል መልዕክተኞች ወደ አሥራ ስድስት የተለያዩ አገራት እንዲሰማሩ በር ሊከፍት ችሏል። ብዙ ፍሬ ያፈሩ አብያተ ክርስቲያንንም አቋቁሞ ነበር።

አገልጋያቸው ወደሌላ ቦታ እስኪዛወር ድረስ አብዛኛውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት ጥቅሙን አይረዱም፤ ከተለያቸው በኋላ ግን ከእነርሱ ጋር ሳለ ይወረውሩበት ከነበረው ድንጋይ የመታሰቢያ ሐውልት ያቆሙለታል።

## ግፊትና ግራ መጋባት

በመንፈሳዊ መረነት አገልግለው የማያውቁ ሰዎች አገልጋይነት በድንግርግር ሁኔታዎች ውስጥ በቀላሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይቶ ማወቅ የሚያስችል ከፍተኛ ልምምድ ይሰጣል ብለው ያስቡ ይሆናል፤ ነገሩ ግን ከዚህ በፍጹም የተለየ ነው። እግዚአብሔር አገልጋዩን የሚቆጥረው ብስለት እንዳለው ዐዋቂ ሰው አድርጎ ነው። ስለዚህም ከዓመታት በፊት ሲሰጠው የነበረውን አመራር ያቆምና ጥቂት ፍንጮችን ብቻ በመስጠት ሌላውን ብዙ ሥራ በራሱ መንፈሳዊ የመለየት ችሎታ ተጠቅሞ እንዲሠራ ይተውለታል። ይህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማወቅ አስፈላጊነት የኃላፊነት ሥራ የሚያስከትለው ድንግርግር ሁኔታ ሲታከልበት ተጨማሪ ሸክም ይሆናል።

አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ የደረሰበትን ለጓደኛው ሲያጫውት እንዲህ ብሏል:- «ግፊት ያለ ልክ እያደገ ይመጣል፤ በየደቂቃው ይለዋወጥብሃል። ለኔ በጣም አዳጋች የነበሩት ከ19041906 ያሉት ዓመታት ናቸው። በከፊል ሙት ነበርኩኝ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሚረዳኝ ሰው ነበረ። ነገር ግን ሌሎች ችግሮች ደግሞ በሌላ በኩል ብቅ ብለዋል። እግዚአብሔር በአንድ በኩል ያለውን ችግር ያቀልልሃል፤ በሌላው በኩል ደግሞ ሌላ አዲስ ነገር ይመጣብሃል።

የክርስትና ሃይማኖት ዓይነተኛ ቁምነገር ግልጋሎት መሆኑን አንድ የቤተ ክርስቲያን ምሁር ተናግሯል። የእግዚአብሔርን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የእግዚአብሔር ልጅ አገልጋይ ሆነ። እያንዳንዱ ክርስቲያንና አብያተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ተልዕኮ መፈጸም እንዲችሉ ይህንን የኢየሱስን ምሳሌ እንዲከተሉ ያስፈልጋል።

እውነተኛ አገልጋይ በተቀዳሚ የሚቆረቆረው ለራሱ ምቾትና ዝና ሳይሆን ለሌሎች ደኅንነት ነው። ከእርሱ አመራር ሥር ለሆኑት ሰዎች በችግራቸው ወቅት ርኅራኄ ያሳያቸዋል፤ ይጠነቀቅላቸዋልም፤ የሚያሳያቸውም ርኅራኄ መጽናኛ የሚሆን እንጂ የሚያዳክም አይደለም። ዘወትርም በጌታ እንዲታመኑ ያስተምራቸዋል። በየአጋጣሚው ሊረዳቸው ዝግጁ መሆኑን ያሳያቸዋል። እግዚአብሔር ሙሴን የሚተካ አገልጋይ ሲመርጥ ታማኝ አገልጋይ መሆኑን ያስመሰከረውን ኢያሱን መምረጡን ማስታወስ ጠቃሚ ነው፤ ዘጸ.33፡11።

የእውነተኛ አገልጋይን ሥራ የተቃና የሚያደርግለት ምሥጢር ለሌሎች በጎ የሚያስብ ሆኖ መገኘቱ ነው። ራሱን ለአገልግሎቱ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበ መሆኑ የሚታየው ራሳቸውን እንደርሱ ላላደረጉ ሰዎች በሚያሳየው ርኅራኄ ነው። በውድቀት ውስጥ ላሉ ወገኖቹ ትዕግሥትና ርኅራኄ ይኖረዋል። ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርሱም ይረዳቸዋል።

ሌላው የመንፈሳዊ አገልጋይ ኃላፊነት ሥነ ሥርዓትን ማስከበር ነው። ይህም ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያጣ ነገር ሊሆን ይችላል። በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ማክበርና ፍቅር የተሞላው ሥነ ሥርዓት አስፈላጊ ነው፤ በተለይም የሃይማኖትን ትምህርት በመጠበቅ፥ በሥነ ምግባርና በክርስቲያናዊ ጸባይ በኩል ይህ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ጳውሎስም የሥነ ሥርዓትን አስፈላጊነት ሲያሳስብ «ወንድሞች ሆይ ሰው በማናቸውም በደል እንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ እናንተ ደግሞ እንዳትፈተኑ ራሳችሁን ጠብቁ» ብሏል፤ ገላ.6፡11። ሥነ ሥርዓትን ለማስከበር በሚወሰደው በየትኛውም እርምጃ በተቀዳሚ አስፈላጊ የሆነው ፍቅር ነው። «እንደ ወንድም ገሥጹት» 2ተሰ.3፡15። «ስለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ እለምናችኋለሁ» 2ቆሮ.2፡8። የራሱን ውድቀት በትክክለኛው መንገድ ያስተካከለ ሰው ትሕትና በተሞላውና እርግጠኛ በሆነ መንገድ ሌሎችን ከውድቀታቸው እንዲነሡ መርዳት ይችላል። በውድቀት ውስጥ ያሉ ሰዎችን በነቀፋና ስህተታቸውን በመጠቆም ከመቅረብ ይልቅ በትዕግሥት ማቅናት ይሻላል።

ሥነ ሥርዓትን የሚመለከቱ ማናቸውንም እርምጃዎች ከመውሰድ በፊት እነዚህን አምስት ነገሮች ማጤን ያስፈልጋል፦

1. እርምጃዎች መወሰድ የሚኖርባቸው ጥልቅ ምርመራ ከተደረገ በኋላ መሆን ይኖርበታል።
2. የሥነ ሥርዓት እርምጃዎች መወሰድ የሚገባቸው ለአጥፊውም ለሌሎችም ጠቃሚ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው።
3. እርምጃዎች መወሰድ ያለባቸው በእውነተኛ የፍቅር መንፈስና አጥፊው የእርምጃ ወሳጆቹን ቅን ሃሳብ በሚረዳበት መንገድ ነው።

የተሳሳትኩት ድፍረት በማጣቴ መሆኑ ያስደንቀኛል። የእግዚአብሔርን መንግሥት ድንበር ሊያሰፉ የቻሉት ሰዎች ድፍረት ያጡ አልነበሩም።»

አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ በአካባቢው ያሉት ሰዎች ጠንቃቃ እንዲሆን የሚያቀርቡለትን ምክር መናቅ የለበትም፤ አስፈላጊ ባልሆኑ ስህተቶች ውስጥ ከመውደቅ ሊያድኑት ይችላሉ። ሃሳቡ ከእግዚአብሔር የተሰጠው መሆኑን ከተገነዘበ የእነርሱን ምክር በመስማት አዳዲስ ነገሮችን በሥራ ላይ ከማዋል እንዳይታገድ መጠንቀቅ አለበት፤ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር እርሱና ተከታዮቹ እንዲራመዱበት ወደሚፈልገው ደረጃ መምራት የሚያስችለውን ድፍረት እንዲያሳጡት ማድረግ የለበትም።

ኃላፊነት መሸከምና ያንን ኃላፊነት በፈቃደኝነት መወጣት የእውነተኛ አገልጋይ ምልክት ነው። አገልጋይ ለዚህ የተዘጋጀ ሰው ካልሆነ ለተግባሩ የሚያስፈልገውን ብቃት ያጣል። በጣም አስቸጋሪ የሆነ ጥረት የሚጠይቁ ተግባራት ለመሸሽ መሞከር አገልጋይ ሌሎችን ለመምራት ያለውን ችሎታ ውሱን ያደርገዋል።

ኢያሱ የአገልጋይነት ችሎታው ያሳየው ታላቁ አገልጋይ ሙሴ በተጓዘበት መንገድ በመራመድና ታላቁን ኃላፊነት ያለማንገራገር በመቀበል ነበር። ከሙሴ ይልቅ ኢያሱ ብቁ ላለመሆኑ ሰበብ መፍጠር ይችል ነበር፤ ቢሆንም ሙሴ የሠራውን ኃጢአት ደግሞ አልሠራም። በዚህ ፋንታ ኃላፊነቱን ወዲያውኑ በመቀበል ራሱን ለሥራው አሳልፎ ሰጥቷል።

ኤልያስ ሲነጠቅ ትቶት የሄደውን ሥራ ማለትም የነቢይነቱን ኃላፊነት ኤልሳዕ ያለማንገራገር ተቀብሏል። ሥልጣንን የተቀበለው ከተወረወረለት ሸማ ነበር፤ ከዚያም የራሱ የሆነ መብት ያለው ነቢይ ሆኗል። በኢየሱስም ሆነ በኤልሳዕ ጉዳዮች ውስጥ ወሳኝ ሆኖ የሚታየው የእግዚአብሔር ጥሪ ነው። ይህን ጥሪ የተቀበለ ሰው ማንም ቢሆን እግዚአብሔር የሰጠውን ኃላፊነት ለመሸከም ማንገራገር የለበትም።

በታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ውስጥ የተከናወኑትን ሥራዎች በጨረፍታ መመልከትና ፍሬያማ መንፈሳዊ አገልጋዮች ያደረጓቸውን ነገሮች ማወቅ ታላቅ ትምህርት ይሰጣል።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ደምቦች በቀድሞው ዘመን የተሠራባቸው ከመሆናቸውም በላይ ለአሁኑም ዘመን አመራር ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡ ናቸው።

- የዕለቱን ሥራ ከመጀመር በፊት ዝግጁ ሆኖ መገኘት ተገቢ አይደለም
- ባለው ጊዜ ተጠቅሞ ለማከናወን መጣር እንጂ በሥራ ብዛት ወይም በጊዜ እጥረት ምክንያት ማጉረምረም አያስፈልግም
- በሚመጡት ደብዳቤዎች ሳቢያ አለማጉረምረም
- ከተከናወኑት ተግባራት የተነሣ ሐሴት ማድረግ እንጂ በከፍተኛ ሥቃይ እንደተሠሩ አድርጎ አለማጋነን
- ከፍተኛ ግምት ሊሰጣቸው ለማይገቡ ተግባራት ትኩረት አለመስጠትና ስለ ሥራ ብዛት ደጋግሞ አለማውሳት

- የአንድን ሰው ሥራ ለመመርመር ከመነሣት በፊት ሰውየውን መውደድ የሚያስችል እውነተኛ ፍቅር ከእግዚአብሔር ዘንድ ማግኘት ያሻል። ለሰውየው ሊሰጠው ስለሚገባው ዕድል መረዳትና የሚያቀርባቸውን ምክንያቶች በትክክል መገምገም አስፈላጊ ነው፤ አለዚያ ምርምሩ ፍሬ ቢስ፥ ትርጉም የለሽና ብጥብጥ ያለ ሊሆን ይችላል

- በሌሎች ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፥ ማንኛውንም ነገር ሳይመረምሩ አለመቀበልና ነገሮችን በቀላሉ ለማንም አለመናገር

- ከበላይ አለቆች ወይም ቀደም ብለው ተመሳሳይ አገልግሎት ከሰዎች ምስጋና፥ ሙገሳና ክብር አለመፈለግ

- ሰዎች ያንተን ምክርና አስተያየት ሳይጠይቁ ወይም ጠይቀው ተግባራዊ ሳያደርጉ ቢቀሩ ቅር አለመሰኘት

- ሌሎችን ዝቅ ወይም ራስህን ከፍ ለማድረግ ከሌሎች ጋር ራስን አለማወዳደር

- ሰዎች ዘወትር ስላንተና ስለ ሥራህ እንዲያወሩልህ አለመመኘት

- ቸርነት ወይም ልዩ ገጸ በረከት አለመፈለግ

- ስህተት የሠራነው በጋራ ነው ወይም ስህተቱ የእርሱ ነው ከማለት ይልቅ የራስን ጥፋተኝነት ማመን

- መሪው በሠራው ሥራ ሌሎች ሲመሰገኑ ያለምንም ቅሬታና ባለመታወክ የሆነውን ነገር በምስጋና መቀበል ነው።

# ምዕራፍ 15

## የአገልግሎት ብቃት መመዘኛ ፈተናዎች

«እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤» ዘፍጥ.22፡1።

«ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፤» ማቴ.4፡1።

አገልግሎት የሚያጋጥሙት ፈተናዎች እንዳሉ ሁሉ የአመራር ችሎታ መለኪያ ፈተናዎችም አሉ። «እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው» የሚለው ዘለቄታዊ እውነት ያለው ታሪክ ነው። ችሎታውን የሚመዝኑ መፈተኛዎች መንፈሳዊ ሥልጣን በተሰጠው በማንኛውም ሰው ላይ የግድ መምጣት አለባቸው።

### የራስን ሃሳብ እየተዉ የሌሎችን ለመቀበል መደራደር

ድርድር ማለት ስምምነት ላይ ለመድረስ የራስን መመሪያዎች በከፊል መተው ነው። ስምምነት ላይ ለመድረስ የራሳችንን ሥነ ምግባራዊ አቋም ብንተው ይህ ጎጂ እርምጃ ነው፤

ብዙ ጊዜ ስምምነት ላይ መድረስ ስንፈልግ ይህንን እንድናደርግ እንጠየቃለን። ይህም ክርስትና ሕይወታችንን በፈተና ላይ ሊጥለው ይችላል።

ሙሴ በጀግንነት ከፈርዖን ጋር ያደረገው ክርክር ድርድር ስለሚያስከትል ፈተና ጥሩ ምሳሌ ነው። እስራኤላውያን ከግብፅ ወጥተው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ሙሴ ቁርጥ ሃሳብ እንደነበረው ፈርዖን ሲረዳ ሙሴን ተስፋ ለማስቆረጥ በሚችልበት መንገድ ሁሉ ተጠቅሟል። በመጀመሪያ ላይ «የምትፈልጉ ከሆነ እግዚአብሔርን አምልኩ፤ ቢሆንም ለዚህ ብሎ ከግብፅ መውጣት አያስፈልግም። ባላችሁበት በታ ሆናችሁ ልታመልኩ ትችላላችሁ» የሚል ሃሳብ አቅርቦለት ነበር። በአሁኑ ጊዜም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ «ሃይማኖት ቸል መባል የለበትም። ቢሆንም በጠባብነት ከዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት ማቋረጥ ተገቢ አይደለም» የሚል ሃሳብ ሊቀርብ ይችላል።

ፈርዖን ያቀረበውን ሃሳብ ተቀባይነት እንዳላገኘ ሲረዳ «ከግብፅ ውጭ ሆናችሁ እግዚአብሔርን በገድ ማምለክ ካለባችሁ በጣም ርቆ መሄድ የለባችሁም፤ ከከተማው ትንሽ ወጣ ብላችሁ አምልኩ» የሚል ሃሳብ አቅርቧል። እንደዛው ሁሉ «ሃይማኖት ጠቃሚና አስፈላጊም ነው፤ ቢሆንም በሃይማኖት ላይ ወገ አጥባቂ መሆን አያስፈልግም፤በተቻለ መጠን ከዓለም ሳይርቁ መኖር ነው» የሚል ሃሳብ ሊቀርብ ይችላል።

ፈርዖን ከዚህ በመቀጠል ያቀረበው ደግሞ «ወንዶቻችሁ ሄደው ያምልኩ ሴቶቻችሁና ልጆቻችሁ ግን አብረዋቸው ባይሄዱ የተሻለ ነው» የሚል ሃሳብ ነበረ። በተመሳሳይ ሁኔታ «ከዓለም ጋር ያለህን ግንኙነት አቋርጥ፤ በዓለም ውስጥ ከሚታየው ዕድገት እንዳትገነጠል በጣም አክራሪ አትሁን» የሚል ሃሳብ ሊቀርብ ይችላል።

ፈርዖን በመጨረሻ ያቀረበው ሃሳብ ከእስራኤላውያን ምኞትና ለዓለማዊ ነገሮች ካላቸው ፍቅር ጋር የተዛመደ ነበር። «መሄድ ያለባችሁ ከሆነ ሂዱ፤ እናንተ ልታመልኩ ስትሄዱ ግን ከብቶቻችሁ ግብፅ ውስጥ መቅረት አለባቸው» ብሏል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ደግሞ «እምነትህ በሥራህ ከምታገኘው ጥቅም ጋር መቃረን የለበትም» የሚለው ሃሳብ ነው።

ሙሴ ከፈርዖን የቀረበውን እያንዳንዱን ሃሳብ በመንፈሳዊ ማስተዋል መርምሯል፤ የሰጣቸውም መልሶች ግልጽና ቁርጥ ያሉ ነበሩ። ሙሴ ለዚህ ጥያቄ «ከእነርሱ አንድ ሰኮናም አይቀርም» የሚል መልስ ሰጥቷል፤ ዘጸ.8፡25+28፤ 10፡11+24+26። ሙሴ ጥራት ያለው አገልጋይ እንዲሆን ለማድረግ የቀረበለትን ፈተና በከፍተኛ ውጤት አልፏል።

## ዝናን ለማግኘት መጠማት

እንደሌሎቹ አገልጋዮች ሙሴም በምኞት ውስጥ የተቀጠበት ጊዜ ነበረ። በሲና ተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረበት ወቅት እስራኤላውያን ወደ ጣዖት አምልኮ ተመልሰዋል። የእግዚአብሔርም ቁጣ ነዷል። እግዚአብሔር ሙሴን «ከርስታቸው አጠፋቸው ዘንድ በቸነፈር እመታቸዋለሁ፤ አንተንም ለሚበዛና ለሚጠነክር ሕዝብ አደርግሃለሁ» ብሎ በዘፀ.14፡12 ላይ ስለ እስራኤላውያን ተናገረው። የእስራኤላውያን ማጉረምረምና አለማመን ለሙሴ ታላቅ ፈተና ሆኖበት ነበር። ከእግዚአብሔር የተሰጠው ተስፋ የእርሱን ሸክም የሚያቀልለትና ከችግሩም የሚያላቅቀው መስሎ ሊታየው ቢችልም እንኳ አይፈረድበትም ነበር።

ሃሳቡን ያቀረበው እግዚአብሔር እራሱ በመሆኑ የሙሴ አመራር የተፈተነበት ሁኔታ ነበር። ሙሴ ራሱን የካደ እንደነበረ የሚያሳይ እግዚአብሔር ላስተላለፈለት መልዕክት ከሰጠው ምላሽ ይበልጥ ምንም ነገር የለም። ይበልጥ የሚቆረቆረው ለእግዚአብሔር ክብርና ለሕዝብ ደኅንነት ነበር። ራሱን ለማበልጸግ ያሰበበት ወቅት ጨርሶ አልነበረም። እግዚአብሔርን በድፍረት ለመቅረብ የጠበቀ ግንኙነት ነበረው፤ ፀምልጃውም አማካይነት በሕዝቡ ላይ ሊደርስ የነበረው ቁጣ ቀርቶላቸዋል።

## መፍትሔ የማይገኝለት የሚመስል ሁኔታ

አንድ ምሁር «አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙት አገልጋዩ ምን ያደርጋል?» በሚለው ጥያቄ የአገልጋዮችን ችሎታ ይመዝን ነበር። አገልጋዮች ከቀላል ሁኔታዎች ይልቅ በአስቸጋሪዎቹ ውስጥ መሥራት ይኖርባቸዋል፤ ምክንያቱም አዳጋች ችግሮች ባላቸው ኃይል እንዲሠሩ የሚያደርጓቸው ከመሆናቸውም በላይ በሌሎች ላይ መታመን ያለባቸው ምን ያህል እንደሆነ እንዲማሩና ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር ማምጣት እንዲችሉ ያደርጓቸዋል። ሌሎች ሊሠሯቸው በሚችሏቸው ጉዳዮች ላይ ጊዜያቸውን መፍጀት አይኖርባቸውም። የእውነተኛ አገልጋይ ችሎታ የሚታየው ዕንቆቅልሽ በተሞሉ ችግሮች ውስጥ የተቻለውን ያህል ሲሠራ ነው።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አገልጋዮች እንደ አሁን ዘመን መሪዎች በቀላሉ ሊታለሉ ከማይችሉ አዳጋች ችግሮች ጋር ፊት ለፊት የተጋፈጡበት ጊዜ አልነበረም ተብሎ ቢነገር ማጋነን አይሆንም። ስለዚህ መሪዎች ተግባሮቻቸውን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ማከናወን በመለማመድ ችግሮችን መፍታት እንደ ቀላል ሥራ መቁጠር ይኖርባቸዋል።

ሙሴ ቀይ ባሕር በደረሰ ጊዜ አዳጋች ችግር ተፈጥሮበታል።

በአንድ በኩል ሊታለፍ የማይቻል ባሕር በሌላውም በኩል ሊታለፍ የማይቻል አሸዋ ከፊቱ ተደቅኖበት ነበር፤ ከፊታቸው ባሕር ከኋላቸው ደግሞ የፈርዖን ሠራዊት ነበሩ። ሙሴ ምንም መውጫ መንገድ በሌለው ቦታ ካስደንጋጭና አጉረምራሚ ሕዝብ ጋር ነበር። በዚህ ባልተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ የሕዝቡ ወኔ ሸሸ። «በግብፅ መቃብር ስላልኖረ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣሽንን?» ብለው አጉረመረሙበት። የእምነት ሰው ሙሴ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ራሱን ከእግዚአብሔር አልለየም። ሙሴ በዚያን ጊዜ የነበረበት ሁኔታ በወቅቱ ተስፋ ቆርጠው ለነበሩት እስራኤላውያን ሕልም መስሎ ታያቸው፤ የሙሴ አቋም ግን የእውነተኛ አገልጋይ አቋም የታየበት ነበር።

ሙሴ ሕዝቡን የሚያስፈራ ነገር እንዳለ ስለተገነዘበ «አትፍሩ» ብሏቸዋል።

የፈርዖን ሠራዊት እየተቃረበ በነበረበት ወቅትም «ቁሙ!» አላቸው። «ቁሙ!» ማለት «ሙቱ!» ማለት መስሎ ሊታይ ይችላል።

እጅግ ሩቅ መስሎ የሚታየውንም «የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ» ማለቱ ነበር፤ ዘፀ.14፡11-13።

ሙሴ በዚህ ወቅት እምነቱን በግልጽ ሊያሳይ የቻለው በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲራመድ ቀርቦለት የነበረውን ፈተና በከፍተኛ ውጤት ስላለፈ ነው፤ እግዚአብሔርም

ደግሞ አክብሮታል። በተስፋ በመሞላት ዛሬ የምታዩዋቸውን ግብፃውያንን ለዘለዓለም አታዩአቸውም» በማለት የተናገረው ትንቢት ተፈጻሚነት አገኘ። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ማዳንና የጠላቶቻቸውን ጨርሶ መጥፋት ተመለከቱ። ከዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር የሕዝቡን መታመን በማየት ሊደረግ የማይቻል የሚመስለውን ሥርቶ ኃይሉንና ጸጋውን ሊገልጽላቸው ዝም የሚልበት ጊዜ እንዳለው መመልከት እንችላለን። አንድ አገልጋይ ከልምምዱ የተማረውን ሲያወሳ እንዲህ አለ፡- «ታላላቅ ሥራዎች ሦስት ክፍሎች አሏቸው። በመጀመሪያ ስንመለከታቸው ልንሠራቸው አንችልም እንላለን፤ ቀጥለን ደግሞ ከዓቅማችን በላይ ሳይሆን አይቀርም ብለን እንገምታለን፤ በመጨረሻም በእምነት ታጥቀን ስንነሣ እርይ አጠናቅቀነዋል ማለት የምንችልበት ደረጃ ላይ እንደርሳለን።»

ስለ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አንድ ጸሐፊ የጻፈው ጽሑፍ እንዲህ ይላል፡- «የሕይወታችሁ ቀይ ባሕር ወደሆነ ቦታ ከደረሳችሁ መውጫ ወይም ሌላ መመለሻ መንገድ ስለሌላችሁ ያላችሁ ዕድል ማለፍ ብቻ ነው። በእናንተ ላይ የወደቀውን የፍርሃት ጨለማ እስኪገፈፍ ድረስ እግዚአብሔርን በመታመን ጠብቁ። እንድትሻገሩ እግዚአብሔር ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ንፋስ ይልክና ውኃውን ይከፍለዋል። እጁም በውኃዎች መካከል ያሳልፋችኋል። የትኛውም ጠላት ሊደርስባችሁ አይችልም፤ የትኛውም ማዕበል አይነካችሁም፤ ጥልቁ ባሕር ሊያሰጥማችሁ አይችልም። በዚህ በጉዟችሁ ውስጥ ብዙ የሚያውኳችሁ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ቢሆንም እናንተ ጌታችሁ ባዘጋጀላችሁ ደረቅ መንገድ በመራመድ ትሻገራላችሁ።

በማለዳ ተነሥታችሁ ወደላይ ርቆ የሚገኘውን ደመና ብትመለከቱ ጌታን ብቻ ታያላችሁ። እርሱ ሲመራችሁ ባሕሩን ትሻገሩና ወደማታውቁት ምድር ትመጣላችሁ። ፍርሃታችሁና ጠላቶቻችሁ ሁሉ ያልፋሉ። ከዚህ በኋላ ፍርሃት አይነካችሁም። ቀድሞ ከነበራችሁበት ቦታ በበለጠ ማለትም እግዚአብሔር ባዘጋጀው ሥፍራ ሆናችሁ ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር ትዘምራላችሁ።»

## ውድቀት

ሥራቸው ሁሉ ተሳክቶላቸዋል ብለን የምንላቸውን ሰዎች ሃሳብ መመልከት ስንችል ሳንደነቅ አንቀርም። በአስተማሪነቱ ወደር ያልተገኘለት አንድ ምሁር በአንድ ታላቅ ስብሰባ ላይ ንግግር ካደረገ በኋላ ሕዝቡ በረከት አግኝተው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ «በእንደዚህ ዓይነቱ ስብሰባ ላይ ሁለተኛ መናገር የለብኝም» አለ። ከአገልግሎት ውጥረት በኋላ ሊመጡ ለሚችሉ ተስፋ የመቁረጥ ስሜቶች ዝግጅት መደረግ አለበት። የማይተኛው ጠላታችን የሰይጣንን ብልሃት የተሞሉ ተንኮሎች ቸል ብለን መዘንጋት የለብንም።

አንድ አገልጋይ ለውድቀቱ የሚሰጠው አፀፋ የወደፊት አገልግሎቱን አቅጣጫ ይጠቁማል። ኢየሱስ ለፍርድ ቀርቦ በነበረበት ጊዜ በጴጥሮስ ላይ ደርሶበት የነበረው ውድቀት በክርስቶስ መንግስት ያለውን የመሪነት ሥፍራ ለዘለዓለም አሳጥቶታል የሚል ሃሳብ ሊሰነዘር ይችል ይሆናል። በዚህ ፋንታ ግን ጴጥሮስ ጥልቅ የሆነ ንስሐ በመግባቱና ለክርስቶስ ያለው ፍቅርም እውነተኛ በመሆኑ ጊዜያዊ ውድቀቱ ሰፋ ላለ አገልግሎት በር ከፍቶለታል። ኃጢአት በበዛበት አጋጣሚ ጸጋ እጅግ አብልጦ በዛ።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተብራራውን የሰዎችን ሕይወት ታሪክ ስናጠና ሁላቸውም ውድቀት የነበረባቸው ሰዎች መሆናቸውን እናያለን፤ አንዳንዶቹ የሠሩት እጅግ ታላቅ የሆነ ጥፋት ነበረ፤

ቢሆንም በውድቀታቸው ተሸንፈው ከተሰጣቸው አገልግሎት ተገልለው ሊቀሩ አልፈቀዱም፤ ውድቀታቸውና ንስሐቸው የእግዚአብሔርን ጸጋ በብቃት የሚያገኙበትን መንገድ ከፍቶላቸዋል። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር በውድቀት ውስጥ ላሉት ልጆቹ ሁለተኛና ሦስተኛ ዕድል የሚሰጥ መሆኑን መግር ችለዋል።

የአገልጋይ ችሎታ መለካት ያለበት በተወሰነ የፈተና ወቅት ባሳየው ውድቀት ሳይሆን በሕይወት ዘመኑ ባከናወናቸው ተግባራት ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ጌታውን ሦስት ጊዜያት ቢክደውም ብርታቱንና ድካሙን የሚያውቀው ጌታ ክርስቲያኑን የሚመሠርትበት ዓለት እንዲሆን መርጦታል።

ዓላማው ግቡን እንዲመታ የሚፈልግ አገልጋይ የደረሰበትን ውድቀት የመጨረሻና የማይደገም አድርጎ መውሰድ የለበትም፤ ውድቀቱ የእርሱም ይሁን የሌሎች በዚህ እምነት ላይ በመመሥረት ሥራውን ያካሂዳል።

## ቅንአት

አንዳንድ ጊዜ ልታይ ልታይ የማለት ጉጉት ያላቸው ቀናተኛና ተርካካሪ ሰዎች ችግር እንደሚፈጥሩ የታወቀ ነው። ሙሴ በሕዝቡ ተቀባይነት አግኝቶ በነበረበት ወቅት ተመሳሳይ ችግር ገጥሞት ነበር። ማጉረምረም ብዙ ጊዜ ሰይጣን የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው።

በጣም የሚያሳዝነው ነገር ሙሴ በዚህ ረገድ በመጀመሪያ ችግር የመጣበት ከሚወዳቸው ከወንድሙና ከእኅቱ ነው። ሙሴ ራሱን በመካድ ለእግዚአብሔር ጥሪ የእምነታ መልስ ባይሰጥ ኖር እሁንም ገና በግብፃውያን ጅራፍ ሥር ነበሩ።

በዚህ ወቅት ማርያም በሕይወቷ ካየችው ልምምድ የተነሣ የቅንአትን አስከፊነት ከእግዚአብሔር ተምራ ማወቅ የነበረባትና በዕድሜዋም የገፋች ሴት ነበረች። በዚህ ፋንታ ግን ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሴት ማግባቱን ሰበብ አድርጋ በመውሰድ ሥልጣኑን ለመቃወም የሹክሹክታ ዘመቻ ጀመረች። በአሁኑ ዘመን የሚታየው የዘር ጥላቻ አዲስ የተፈጠረ ክስተት አይደለም። በዚያም ወቅት የሙሴ እኅት በወንድሟ ሚስት መበለጥን እጥብቃ ተቃውማለች፤ ደካማውን አሮንንም የዚህ ዓመፅ ተባባሪ አድርጋዋለች።

ማርያምና አሮን ሙሴን በመተካት መሪ ሊሆኑ መፈለጋቸው ግልጽ አይደለም፤ ያካሄዱት የነበረው ሰይጣናዊ ተግባር ግን ሙሴ ያለውን ተቀባይነት የሚያሳጣ ነበር። ቅናታቸው ለእግዚአብሔር የቀኑ በማስመሰል የቀረበ ነበር። ስለዚህም «እግዚአብሔር የተናገረው በሙሴ ብቻ ነውን? በእኛስ አልተናገረምን?» ብለዋል። ሙሴ እግዚአብሔርን በመወከል ለሕዝቡ ለመናገር ያለውን ተሻሚ የሌለበት መብት ለመቀበል እምቢተኛ ሆነዋል።

ሙሴ በዚህ ወቅት የፈጸመው ድርጊት በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ሁኔታው እጅግ ቢያቆስለውም ራሱን ለማመጻደቅ ምንም አልተናገረም፤ ሙሴን የሚቆረቁረው የራሱ ዝና ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር ነበር። «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ» ተብሎ በዘኁ.12፡3 የተነገረለት በዚህ ወቅት ከፈጸመው ድርጊት የተነሣ ነበር። ሙሴ ሁኔታውን በትዕግሥት በመመልከት ዝም ቢልም እግዚአብሔር በአገልጋዩ ሥልጣን ላይ የተቃጣውን ቅንአት ሊያልፈው አልፈለገም።

በሰው ፊት በግልጽ የታየ ጥፋት ስለሆነ እንዲሁ በአደባባይ ፍርድ ሊሰጥበትና ቅጣት የሚገባው በደል ነው። «እነሆም ማርያም ለምጻም ሆነች፤ እንደ አመዳይም ነጭ ሆነች» የሚለው የደረሰባትን ቅጣት የሚያሳየው መግለጫ በዚያው ታሪክ ውስጥ ቀርቧል። ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው ይህ አሰቃቂ ቅጣት እግዚአብሔር የቀባው አገልጋይ ምንም ያህል ደካማና ውድቀት ያለበት ሰው ሆኖ ቢገኝም በእርሱ ላይ መነሣት ምን ያህል አሳዛኝ ኃጢአት መሆኑን ለማሳየት ነው። በዚሁ ታሪክ ውስጥ ሌላው የሙሴ ታላቅነት ይታያል፤ ሙሴ በእኅቱ ላይ የደረሰውን ተመልክቶ ለእኅቱ መማለድ ጀምሯል፤ እግዚአብሔርም ለእርሱ ጸሎት ታላቅ መልስ ሰጥቷል።

መንፈሳዊ አገልጋይ ከዚህ የሚያገኘው ግልጽ ትምህርት አለ። እግዚአብሔር በኃላፊነት ላይ ያስቀመጠው ሰው በቅንአት የተነሣሡ ባላንጣዎች ሲቃረኑት ራሱን ለማጽደቅ መነሣት የለበትም። ሰማያዊ ጠባቂው እግዚአብሔር በእጆቹ ይጠብቀዋል፤ በማርያም ላይ የደረሰው ተግሣጽ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። እግዚአብሔርም «በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም?» በማለት የተናገረው ለዚህ ነው።

ቆሬ የተባለውም ሰው በሙሴና በአሮን ላይ በምክንያት የለሽ መንገድ በቅናት ተነሥቶ ነበር። ከፍተኛው ሥልጣን ለእነርሱ ብቻ የተሰጠው ለምንድን ነው? ከእነርሱ እኩል የሆኑ ሌሎች ሰዎች የሉም ማለት ነው? የእግዚአብሔርን መልዕክት ማምጣት የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው? የሚል ሃሳብ አመንጭቷል። «ማኅበሩ ሁሉ እያንዳንዳቸው ቅዱሳን ናቸው፤ እግዚአብሔርም በመካከላቸው ነው፤ እናንተ እጅግ አብዝታችሁታል፤ በእግዚአብሔር ጉባዔ ላይ ለምን ትታበያላችሁ?» ብለዋል፤ ዘኁል.16፡3።

ሙሴ አሁንም ራሱን አላመጻደቀም፤ እግዚአብሔር በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ በቅንአት በተነሡት ሰዎች ላይ ጻድቅ ፍርድ ሰጠ። በሕዝቡም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው፤ የሙሴም ዝና ከቀድሞው ይልቅ እጅግ ገነነ።

እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ለመረጣቸውና ለሾማቸው አገልጋዮቹ ቀናተኛ ነው። ያከብራቸዋል፤ ይጠብቃቸውማል፤ ያጸድቃቸዋል፤ መብታቸውን መንከባከብ እንደሚያስፈልጋቸው ያስተምራቸዋል።

# ምዕራፍ 16

## ለሌሎች የአገልግሎት ድርሻቸውን ማከፋፈል

«ሙሴም ከእሥራኤል ሁሉ አዋቂዎችን መረጠ፤ በሕዝቡም ላይ ... አለቆች አድርጎ ሾማቸው፤» ዘፀ.18፡25።

ለአገልጋይነት ከሚሰጡት ትርጉሞች አንዱ የሌሎችን ልዩ ችሎታና ዓቅም በማወቅና በመገንዘብ በተገቢና በአመቺ ቦታ ማስቀመጥ የሚለው ነው። ሥራዎች በሌሎች ሰዎች አማካይነት በፍሬያማ መንገድ እንዲከናወኑ የማድረግ ችሎታ ያለው አገልጋይ ከፍተኛ የአገልጋይነት ችሎታ አለው ማለት ነው። የሺህ ሰዎችን ሥራ ከመሥራት አንድ ሺህ ሰዎችን

ማሠራት የተሻለ ነው። ሰውን ሊሠራ በሚችልበት ቦታ አስቀምጦ ተገቢውን ሥልጣን መስጠት የእውነተኛ አገልጋይ ተግባር ነው።

ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎች እንዳሏቸው ተገንዝቦ በተገቢው ቦታ ተቀምጠው እንዲሠሩ ማድረግ ከፍተኛ ችሎታ ነው። ይህ ችሎታ ለሥራ ብቁ ያልሆነ ሰው በአንድ ተግባር ላይ ከማሰማራት የተነሣ ከሚፈጠር ተስፋ መቁረጥ አገልጋዩን ያድነዋል።

ብዙ ጊዜ ኃላፊነት የሚሰጡ ሰዎች ኃላፊነቱን የሚሰጡት አስፈላጊ ከሆነው ሥልጣን ጋር አይደለም። ከኃላፊነት ሸክም ለመገላገል ኃላፊነቱን መስጠት ይፈልጋሉ፤ ሥልጣን ለመስጠት ግን አይፈቅዱም። ይህ ለበታች ሠራተኞች መልካም አይደለም፤ ፍሬያማ ሊሆንም አይችልም። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት መተማመን የሌለ መሆኑን እንደሚያመለክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። መተባበርንም ሊያስገኝ አይችልም። አገልጋይ ሊሆን ለሚሠለጥነው ሰውም አስፈላጊውን ኃይል አይሰጠውም። በእርግጥ ኃላፊነት የተረከበው ሰው እንደሰጪው ሆኖ ሊሠራ አይችልም ይሆናል፤ በዚህም ምክንያት ደግሞ ኃላፊነት የሚሰጠው ሰው ሥልጣን እንዲነፈገው አያሻም። ኃላፊነትን መረከብ የሚማረው ወጣት በዘመኑ ያሉትን ሰዎች አኗኗር በሚገባ የተረዳ ስለሚሆን ሥራውን በበለጠና በተሻለ መንገድ ሊያከናውን ይችል ይሆናል። ኃላፊነት ሲሰጠው ሥልጣን አብሮት ካልተሰጠው እንዴት አድርጎ ልምምድ ሊያገኝ ይችላል? በመጨረሻስ እንዴት አድርጎ ሥልጣን ይቀበላል?

በአገልጋይነት የተቀመጠ ሰው ሌሎች እርሱን እንዲወክሉት ማድረግ አለመቻሉ በራሱ ላይ ሥራ እንዲበዛበት ከማድረግ አልፎ የራሱን ኃላፊነት እንዳይወጣ ያደርገዋል። ከበታቹ ያሉት የአገልጋይነት ችሎታ ያላቸው ሰዎችም እንዳይሠሩ ያደርጋል። እኔ በተሻለ መንገድ ሥራውን እሠራዋለሁ ብሎ የሙጢኝ ማለት የሚያሳየው የአመራርን ውሱንነት ብቻ ሳይሆን በራስ መመካትንም ጭምር ነው። ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር አገልጋይ አገልግሎቱ ከልክ ያለፈ ፍሬያማ ይሆናል።

አገልጋይ ሌሎችን ወኪል ካደረገ በኋላ በእነርሱ ላይ የሚተማመን መሆኑን ማሳየት አለበት። ለእነርሱ ነፃነት መስጠትና ተሰጥዎአቸውን በተግባር እንዲገልጹ ዕድል መስጠት አለበት።

አገልጋይነት በውክልና የተሰጣቸው ሰዎች ግባቸውን ሊመቱ አለመቻላቸው የሚያሳየው ኃላፊነት የሰጣቸውን ሰው ድክመት ነው፤ ምክንያቱም ለዚያ ኃላፊነት የመረጣቸው እርሱ ስለሆነ ነው። የበታች ሠራተኞች የሚሠሩትን ማናቸውንም ተግባር በተሰጣቸው መመሪያ እስካከናወኑት ድረስ ውጤቱ የፈለገው ዓይነት ቢሆንም የመሪያቸውን ድጋፍ ማግኘት አለባቸው። የሠራተኞቹ ኃላፊነት በግልፅ የታወቀ መሆን ያስፈልጋል ይህም አለመግባባት እንዳይፈጠር በጽሑፍ መስፈር አለበት። ብዙዎች በዚህ ዓይነቱ መንገድ ባለመጠቀማቸው ብዙ ውድቀቶች ተፈጥረዋል።

በዘጸአት 18፡1-27 ተጽፎ የሚገኘው ዮቶር ለሙሴ የሰጠው ምክር ኃላፊነትንና ሥልጣንን ለሌሎች ወኪል አድርጎ ስለመስጠት የሚናገር ጥሩ ምሳሌ ነው።

እስራኤላውያን በግብፅ የኖሩት ምንም ዓይነት ኅብረት የሌላቸው የተበታተኑ ባሪያዎች ሆነው ነበር። ሙሴ በነበረበት ዘመን ግን ራሳቸውን የቻሉ ሕዝብ መሆናቸው እየታወቀ ሄዷል። የተደራጀ ሕዝብ መሆንም ጀምረዋል። ከዚህ ዕድገት የመነጨው አስተዳደርን በተገቢው

መንገድ የመምራቱ ተግባር በሙሴ ላይ ስለወደቀ ዮቶር ሙሴን ሊመክረው ተነሥቷል። ሕዝቡ አዲስ ኅብረት ስለመሠረቱ ሙሴ ከንጋት እስከ ምሽት የእነርሱን ጉዳይ በማዳመጥና ፍርድ በመስጠት ሊያሳልፍ ተገዷል። ሙሴ ሕግንና ፍርድን የሚመለከቱ ተግባራት ማከናወኑ ግዴታው ነበር። እርሱ ሲሰጣቸው የነበሩትም ፍርዶች እንደ እግዚአብሔር ቃል ይቆጠሩ ነበር።

ሙሴ ይህንን ተግባር በማከናወን ሊገፉ እንደማይችል ዮቶር ተመለከተ፤ ከኃላፊነቱም ከፊሉን ለሌሎች በውክልና እንዲሰጥ ለማድረግ ሁለት ምክንያቶች አቀረበለት። በመጀመሪያም በቁጥር 18 «ይህ ነገር ይከብድብሃል» የሚል ምክንያት ሲሰጠው ይታያል። አንድ ሰው ሊያከናውን የሚችለው የጉልበትም ሆነ የአዕምሮ ተግባር መጠን የተወሰነ ነው። ከዚያ ገደብ አልፎ መሥራት ተገቢ አይደለም። በሁለተኛ ደረጃ ሙሴ በዚያን ጊዜ ሲሠራ የነበረው ሥራ የተፈለገውን ያህል ፍጥነት አልነበረውም፤ ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ የሚፈልጉትን ያህል ትኩረት ሊሰጣቸው ስላልቻለ እርካታ አጥተዋል። ኃላፊነትን ለሌሎች በማካፈል ውሳኔ የሚያሻቸው ሕግ ነክ ተግባራት በፍጥነት እንዲከናወኑ ማድረግ ይቻላል፤ ሕዝቡም በዚህ ይረካሉ፤ ቁጥር 23።

ስለዚህ ዮቶር ሁለት ሃሳቦችን አቅርቧል። ሙሴ የእግዚአብሔር ተጠሪ ሆኖ ሥራውን መቀጠል አለበት፤ መንፈሳዊ መመሪያዎችን የማስተማሩ ተግባር የእርሱ መሆን አለበት። ከባድ ሆነው የተገኙ ጉዳዮችን ወደ እግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ያለበትም እርሱ ነው፤ ቁጥር 16፥1920። ፍርድ የመስጠቱን ተግባር ግን የእርሱን ሸክም ሊያቀሉለት ለሚችሉ ሰዎች ማከፋፈል ይኖርበታል። ሙሴ ከሥራ ብዛት የተነሣ ሕይወቱ ቢያልፍ በሥልጣን መጠቀምንና ኃላፊነትን መሸከም የተለማመዱ ሰዎች ሳይተው ስለሚሞት ይህ ምክር ብልሐት የተሞላው ነው ለማለት ይቻላል። ተተክተው ሊሠሩ የሚችሉ ሰዎች አለማዘጋጀት ለብዙ የእግዚአብሔር ሥራዎች ውድቀት ምክንያት ሆኗል።

ሙሴ የዮቶርን ምክር ስለተከተለ ብዙ ጥቅም አገኘ። እርሱን ለሚመለከቱት ከፍተኛ ኃላፊነቶች ትኩረት መስጠት ቻለ። ተደብቆ የኖረውና ሳይታወቅ የቆየው የብዙዎች ችሎታም በግልጽ ሊታይ ችሏል። ሙሴ ያን ሁሉ ተግባር ብቻውን ማከናወን ቢቀጥል ኖሮ የእርሱ ተቀናቃኝ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩት፥ ተሰጥዖ ያላቸው የእነዚህ ሰዎች የኃላፊነትን ቀንበር የመሸከም ችሎታ ማደግ እንዲችል በር አይከፈትለትም ነበር፤ የሙሴም ደጋፊዎች አይሆኑም ነበር። ሕግን የሚመለከቱ ተግባራት በመከናወናቸው ሰዎችን ሊያሳዝኑ የሚችሉ ነገሮች ተወግደዋል። ሙሴ ይህንን በማድረጉ እርሱ ከሞተ በኋላ ሕዝቡን በፍሬያማ መንገድ የመሩትን ሰዎች ለማሠልጠን በር ከፍቷል።

ዮቶር በዘጸአት 18፡23 ውስጥ «ይህንም ብታደርግ እግዚአብሔር እንዲሁ ቢያዝዝህ መቆም ይቻልሃል» እያለ ሙሴን ሲያደፋፍረው እንመለከታለን፤ ይህ ጊዜ የማይለውጠው ሐቅ ነው። ዮቶር የሰጠው ምክር የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተደገፈ ነበር። እዚህ ነጥብ ላይ እግዚአብሔር ራሱ ለመረጣቸው ባሮቹ ተግባራቸውን ማከናወን የሚያስችል ኃላፊነት ይሰጣቸዋል የሚል መመሪያ እንዳለ መመልከት እንችላለን። ከእኛ ይልቅ በተሻለ መንገድ ሥራዎችን ማከናወን የሚችሉ ሰዎች ይኖራሉ፤ ለእነዚህ ሰዎች ሥራውን መስጠት ይኖርብናል። እነዚህ ሰዎች ከእኛ በከፋ ሁኔታ ሥራውን ቢሠሩት እንኳ ልንሰጣቸው ይገባል። ሙሴ ከመረጣቸው ከሰባዎቹ ሰዎች ይልቅ እራሱ በበለጠ መንገድ መሥራት ይችል ነበር። እርሱ ብቻውን ሥራውን መሥራት ቢቀጥል ግን የእርሱ ማንነት ብቻ ሲታወስ ይኖር ነበር።

ዮቶር ለሙሴ የጠቆማቸው ረዳቶችን የመምረጫ መንገዶች እራሳቸው መንፈሳዊ የመለየት ችሎታ ለመኖሩ ማስረጃ ናቸው። እነዚህ ሰዎች የሚረከቡት ተግባር ትክክለኝነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ችሎታ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል። እግዚአብሔርን የሚፈሩና ወገኖቻቸውንም የሚያከብሩ መሆን ይገባቸዋል፤ ከመመኘት የራቁና በጉቦኝነት የማይጠረጠሩ እንዲሆኑ ያስፈልጋል።

በዚህ አጋጣሚ አገልጋዮች ሊማሩ ከሚገቧቸው ቁምነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል። ብቃት ባለውና እርካታ በሚሰጥ መንገድ ልናከናውን ከምንችለው በላይ ሥራዎችን መያዝ ስህተት ነው። ከድርሻችን በላይ የሆነ ሥራ መሥራት ዋጋ የለውም። የራሳችንን ልክ ማወቅና መገንዘብ መልካም ነው። እኛን እንደ ዮቶር ሆኖ የሚመለከተን ሰው ከእኛ ይልቅ የሥራችንን መብዛት ሊመለከት ይችላል፤ በአገልጋይነት ሥፍራ ለመሥራት የምንከፍለውን ዋጋ ስለሚመለከት የእርሱን ምክር ልናስተውል ይገባል። በእግዚአብሔር አገልግሎት ምክንያት እንኳ የተፈጥሮ ሕጎችን ብንጥስ ከቅጣት አናመልጥም። ከእግዚአብሔር መመሪያ በማግኘት ሳይሆን በሰዎች ግፊት ኃላፊነትን መቀበል ይቻል ይሆናል። እግዚአብሔር ለእነዚህ ዓይነት ተግባራት ተጠያቂ አይደለም።

የወንጌል መልዕክተኞች ከሚፈተኑባቸው ችግሮች አንዱ ለአገልግሎት የተሰማሩበት ሀገር ሰዎች ኃላፊነት ለመቀበል መንፈሳዊ ብስለት ሲያገኙ ኃላፊነትን አለመስጠት ነው። ይህ ኃላፊነትን ለሌሎች የመስጠት ተግባር ወንጌላውያን በሚሠሩበት ሀገር ውስጥ ያሉትን ሰዎች የተደበቀ የመሪነት ችሎታ ከተቀበረበት ለማውጣትና ለማሠልጠን ያለባቸው ኃላፊነት ፍጻሜ ነው። በዚህ ወቅት ጥበብ የተሞላው አስተዋይነት ያስፈልጋል፤ ጣልቃ መግባት የሚያሻው አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ሰዓት ብቻ ነው። አድፍጦ መጠበቅ በራስ መተማመንን ያጠፋል።

የአንድ ትልቅ የወንጌል አገልግሎት ተቋም ዋና ጸሐፊ የነበረ አገልጋይ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ያለውን ሥራ ባሉት ሠራተኞች ልክ ከፋፍሎ ለእያንዳንዱ ሰው ኃላፊነት በመስጠት ሥራውን ሁሉ ብቻውን የመቆጣጠር ተግባሩን አቋርጧል። የሥራ ባልደረቦቹንም ሙሉ በሙሉ በመተማመን ያለ ምንም ቅሬታ ሥልጣኑን አከፋፍሏል። ስለዚህ ሰው የሚከተለው ተነግሮለታል፡- «ይህ ሰው ስለ አገልግሎት የተረዳው ነገር ቢኖር ሥልጣንን ለሌሎች ማከፋፈልና ጥንቃቄ በተሞላው አኳኋን ረዳቶችን መምረጥ ነበር። ይህንን ዓይነት ተግባርም በማከናወን ረገድ አቻ አይገኝለትም ነበር።»

እንዲሁም ስለ አንድ ሌላ የወንጌል አገልግሎት ተቋም መሪ የሥራ ባልደረባው ከዚህ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቷል፡- «በሥሩ ይተዳደሩ በነበሩት ሠራተኞች ሥራ ውስጥ ጣልቃ የማይገባ ከፍተኛ የመምራት ተሰጥዖ የነበረው ሰው ነበር። እያንዳንዱም ሰው የግሉን ሥራ እንዲሠራ ነፃነት ይሰጥ ነበር።»

ሌላው ባልደረባው ደግሞ፡- «ሰዎች ምን ሊሠሩ እንደሚችሉ የማወቅ ችሎታ የነበረውና ይህንንም በተግባር ሲያውሉት በማየቱ ማረጋገጫ ያገኘ ሰው ነበር። ሰዎች ባገኙት ዕድል ተጠቅመው የቻሉትን ያህል እንዲሠሩ በመፍቀድ በስህተት ላይ እንዳይወድቁ ብቻ ይጠባበቃቸው ነበር» ብሏል።